# እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ
## 1ኛ መጽሐፍ

ትርጉም:- መስፍን ወልደአማኑኤል
እርማት:- በዮሴፍ መና

አሳታሚ
ቸርች ዳይናሚክስ ኢንተርናሽናል ከኢ ስሪ ፓርትነርስ ሚኒስትሪ ኢትዮጵያ
እና ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ጋር በመተባበር የተዘጋጀ
መጋቢት ወር 1998 ዓ.ም.

© የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ይህንን መፅሐፍ ለመጠቀም የሚቻለው:-
አንድ ለአንድ ለሚደረግ የክትትልና የደቀ መዝሙርነት ሂደት ብቻ ነው።
ለአነስተኛ ቡድን ጥናት፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ
ትምህርት ቤት፣ለኤሚናሪ፣ ወዘተ... መጠቀም የተከለከለ ነው።

Originally published under the title of KNOWING GOD PERSONALLY by Multiplication Ministries, P.O.Box 1279, Vista, CA 92085, 1996.

# መግቢያ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠን ሥራ አንድ ብቻ ነው (ማቴ. 28:18-20):: ይኸውም «ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው» ነው::

ስለሆነም የወንጌል መልእክተኞች፣ መጋቢያን፣ መሪዎችና የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ቀዳሚ ተግባር የምናደርገው ጉዳይ ነው:: ይህ ብቻ ሳይሆን መደበኛ ተግባር ወንጌልን በመመስከር ደቀ መዛሙርትን የማፍራት ሂደት ነው::

በተለይ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ አምነን ድነን መሪ አገልጋዮች መሆናችንን ሊያውቁን የሚችሉት በሹመት ወይም ተሰይመን በተሰጠን ኃላፊነት በምንፈጽማቸው ተግባራት ሳይሆን በፈቃደኝነትና ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ተግባራችን ነው::

ስለዚህ በምንገኝበት የአገልግሎት ተቋማት ሆነ በየቤተ እምነታችን በተሰጠን መንፈሳዊ በሚመስሉ ሥራዎች ተጠምደን ክርስቶስ ካዘዘን ደቀ መዛሙርት አድርጉ ከተባልንበት ወጣ ብለን እንዳንገኝ መጠንቀቅ ይኖርብናል::

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን ራዕይ | 1-19 |
| እግዚአብሔርን በግል ማወቅ ደቀመዝሙር አድራጊ መመሪያ | 20-24 |
| የማያቋርጥ የጽሞና ጊዜ እንዴት ሊኖረኝ ይችላል | 24-27 |
| ትምህርት አንድ - ከእግዚአብሔር ጋር መጀመር | 28-35 |
| ትምህርት አንድን በግል ሕይወት መተግበር | 37-40 |
| ትምህርት አንድ የደቀመዝሙር አድራጊ መመሪያ | 41-44 |
| ትምህርት ሁለት - ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ | 45-53 |
| ትምህርት ሁለትን በሕይወት መተግበር | 53-57 |
| ትምህርት ሁለት የደቀመዝሙር አድራጊ መመሪያ | 58-60 |
| ትምህርት ሶስት - ለእግዚአብሔር የመኖር ኃይል | 61-68 |
| ትምህርት ሦስትን በሕይወት መተግበር | 69-73 |
| ትምህርት ሦስት የደቀመዝሙር አድራጊ መመሪያ | 74-77 |
| ትምህርት አራት - እንደ እግዚአብሔር ልጅ ማደግ | 78-85 |
| ትምህርት አራትን በግል ሕይወት መተግበር | 85-91 |
| ትምህርት አራት የደቀመዝሙር አድራጊ መመሪያ | 91-95 |

# ደቀመዝሙር አድራጊ የወንጌል ማኅበርተኛ ቤተክርስቲያን

| |
|---|
| **ዓላማ**:- ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን ዓላማ የምስራቹን ወንጌል ላልሰሙት ሁሉ በምእመናን አማካኝነት በማድረስ የዳኑትን የክርስቶስ እውነተኛ ደቀመዛሙርት አድራጊዎችና የወንጌል ተልእኮ ማኅበርተኞች በመሆን በተመሳሳይ ተግባር ሂደት እንዲሳተፉ ማድረግ ነው፡፡ |

## ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን

ሁለት አስፈላጊ ጥያቄዎች:

1. ቤተክርስቲያን የማን ናት?
2. የቤተክርስቲያን ዓላማ ምንድን ነው?

### ቤተክርስቲያን የማን ናት?

ማቴ. 16:13-18 «አንተ ክርስቶስ ነህ. . . በዚች አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ. . .»

1 ቆሮ. 3:10-11 « . . . ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»

1ጴጥ. 2:4-6 «. . . የተመረጠውንና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም»

ኤፌ. 1:22-23 «ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተክርስቲያን ሰጠው እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላት ናት፡፡»

## የቤተክርስቲያን ዓላማ ምንድን ነው?

**1. የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ በሕይወቱ ሲገለጽ**

ዮሐ. 1:29 « እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ. . .»

ሉቃ. 19:10 « የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና።»

2 ጴጥ፣ 3:9 « ጌታ ስለተስፋ ቃሉ አይዘገይም ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።»

**2. የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ በደቀመዛሙርቱ ሕይወት ሲገለጽ**

ማር. 1:17 « በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ።»

ሉቃ. 14:26-27፣33 « ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።»

« ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም»

ማቴ. 7:21 « በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።»

ዮሐ. 15:1-2 «. . . ፍሬ የሚያፈራውን ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል»

ዮሐ. 15:8 « . . . ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀመዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል»



ዮሐ. 15:16 « . . . እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም. . . ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ»

**3. የክርስቶስ ዓላማ ለቤተክርስትያን ደቀመዝሙር ማፍራት ነው**

ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው:- *«ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።እንግዲህስ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።»* ማቴ. 28:18-20

**«ትዕዛዙ ደቀመዛሙርት አድርጉአቸው» ነው**




**በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ደቀመዛሙትን የማፍራት ሂደት ምን ሊመስል ይገባል?»**




የተሳካ ደመዛሙርትን የማፍራት ሂደት መረን የመገንባት ሂደት ነው!

# ቤተክርስቲያን ልትከተል የሚገባት ደቀመዝሙርትን የማፍራት ራዕይ

«ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬያችሁም ሊኖር ሾምሁአችሁ»
ዮሐ 5:16

ዓላማው:- «ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተክርስቲያን የሚፈልገው ወንጌል እንድታበስርና ደቀመዛሙርቱን እንድታፈራ መሆኑን መግለጽ ነው::»

## ሀ/ ቤተክርስቲያን የማን ናት?

ማቴ. 16:13-18 የዚህ ጥያቄ መልስ ይሆናል:: በዚህ ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው:: በቁጥር 13 «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቃቸው በቁጥር 14 ደቀመዛሙርቱ የሚከተሉትን መልሶች ሰጡት «እነርሱም አንዶንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ ሌሎችም ኤ ልያስ ሌሎቹም ኤርሚያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው? ይላሉ የተሳሳተና ከእውነት የራቀ እንደሆነ ያመለክታል:: በመሆኑም ኢየሱስ ጥያቄውን ወደ ደቀመዛሙርት አዞረና በቁጥር 15 ላይ እንዲህ አለ «እርሱም እናንተስ እኔን ማን እንደሆነሁ ትላላችሁ አላቸው» ስምዖን ጴጥሮስም በቁጥር 16 የሚከተለውን መልስ ሰጠ:: «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» አለ::

ይህ ምላሽ በጊዜው የነበሩ ሰዎች ከሰጡት መልስ መረዳት እጅግ የላቀና ጥልቅ መሆኑን ያመለክታል:: በቁጥር 17 መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ የጴጥሮስ መልስ ከሥጋና ከደሙ ሳይሆን ከሰማያዊ አባት እንደተገለጠለት ሲናገር ኢየሱስ ጴጥሮስን እንዲህ አለው:-



«እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ የገሀነም ደጆችም አይችሏትም»
ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስ ስለ እርሱ የተናገረው ቃልና የመለሰው መልስ ሙሉ በሙሉ ትክክል እንደሆነ መቀበሉን ሲያ ረጋግጥ እርሱ በተናገረው በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ የእርሱ ከኢየሱስ የሆነውን ቤተክርስቲያን እንደሚሰራ ተናገረ:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር ቤተክርስቲያንን እሰራለሁ ወይም የኛን ቤተ ክርስቲያን እሰራለሁ አላለምና ያለው ቤተክርስቲያኑን እንደሚሰራ ነው:: ከዚህም ሌላ በኤፌ 1:22-23 ላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሳቱን መናገሩ ራሱ የቤተ ክርስቲያን ብቸኛ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለመግለጥ እንዲህ አለ:-
«ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተክርስቲያን ሰጠው እርሱዋም አንዱና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት» አለ:: እንዲሁም ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌ 5:3 ላይ ለባልና ሚስት በተናገረ ጊዜ «ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስቱ ራስ ነውና::» ይላል::

ስለዚህ «ቤተክርስቲያን የማን ናት?» ለሚለው ጥያቄ የቤተ ክርስቲያን ባለቤት ያለምንም ማወላወል እግዚአብሔር ወልድ የዓለም ሁሉ ፈጣሪና የሁላችን አባትና አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ስለሆነም የቤተክርስቲያን ዓላማ ምንድር ነው? ለሚለው ጥያቄም መልስ መስጠትና ውሳኔ መስጠት የሚችል ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ብቻውን ነው::

**2ኛ. የቤተክርስቲያንን ዓላማ መረዳት ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተ ክርስቲያንን የመመስረት መመሪያ ነው::**

**ለ. የቤተክርስቲያን ዓላማ ምንድር ነው?**

የክርስቶስ ዓላማ ለቤተክርስቲያን ምን እንደሆነ መረዳት አስቸጋሪ አይደለም:: ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ዓላማ ግልጽ በማድረጉ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ያለውን ዓላማ በትክክል ለመረዳት ከፈለግን የሚከተሉት ደረጃዎችን ጠብቀን መመልከት ይገባናል:: እነርሱም:-

ሀ/ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ለሕይወቱ ምንድር ነው?
ለ/ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ለደቀመዛሙርቱ ምንድር ነው?
ሐ/ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ለቤተክርስቲያኑ ምንድር ነው?
የሚለውን ሐሳብ ተራ በተራ ልንመለከት ይገባናል::

1. **የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ለሕይወቱ በሚከተሉት መንገዶች ተገለጸ::**

- በዮሐ. 1:29 መሰረት «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» በመባል መገለጹ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ለሕይወቱ ለምድር ወገኖች ሁሉ ኃጢአት መስዋዕት ቤዛ ሆኖ ዓለምን ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ማሸጋገር መሆኑን ነው::
- በሉቃ. 19:10 መሰረት «የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቷልና» በመባል መገለጹ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ለሕይወቱ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዋናው ምክንያት የጠፋውን በመፈለግና በማዳን ለዘላለም ሕይወት ማብቃት መሆኑን ነው:: ይህ የሚያመለክተው ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር የሚስማማ ዓላማ መኖሩን የሚያስመሰክረው በሰዎች መዳን ላይ ሲያተኩር መሆኑን ነው::



- በ2ኛ ጴጥሮስ 3:9 ላይ «ለአንዳንዶቹ የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለእናንተ ይታገሳል» ይላል:: ይህ ሐሳብ የክርስቶስ ዓላማ ለሕይወቱ ሁሉም ወደ ዘላለም ሕይወት እንዲገባ እንጂ እንዳይጠፋ ሲል መታገሱን ያመለክታል:: ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስን የትዕግስት ዘመኑን ለፈጣን የምስራች ወንጌል ስራ ሩጫ ልትጠቀም እንደሚገባት ይጠቁማል::

2. **የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ ለደቀመዛሙርቱ በሚከተሉት መንገዶች ተገልጸአል::**

- በሉቃ. 14:26-27 ላይ «... ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱን እና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እህቶቹንም የራሱን ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም:: ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም» ይህ ማለት ክርስቶስን በሕይወት ወስኖ መከተል የሚያስከፍለው ዋጋ ቢተመን ከአባት ከእናት ከሚስት ከልጅ ከወንድምና ከእህት ብሎም ከራስ ሕይወትም በላይ መሆኑን ያስገነዝባል:: ስለዚህ ቤተክርስቲያን ሰዎችን የክርስቶስ ደቀመዝሙርት የማድረግን እውነተኛ አገልግሎት የምትሰጥ ከሆነ ሊመጣ ያለውን የዘላለም ተስፋ እንጂ በምድር ከማናቸውም ጠቃሚና ደጋፊ ከሚመስለው ጋር ያልተደበላለቀ አገልግሎት እንድትሰጥ ይጠበቅባታል ማለት ነው::

- በሉቃ. 14:33 ላይ «እንግዲህ እንደዚህ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀመዝሙር ሊሆን አይችልም» ይላል:: ከዚህ ክፍል አንድ የክርስቶስ ተከታይ ሊሆን የቀረበ ሰው የራሱን ሕይወት ከምንም ጋር እያጋራ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መስጠት እንደሚገባው ነው:: ስለዚህ የምንሰብከው የወንጌል መልዕክት ሰዎች በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የወንጌል መልዕክት ሰዎች በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን መዳንና የዘላለም በረከት ላይ እንጂ በምድር የሚያልፍ ብልጽግና ማንጸባረቅ እንደሌሰብን ነው::
- ማቴ. 7:21-23 ላይ «በሰማያት ያለውን የአባትን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም:: በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ በዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል:: የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመጸኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባችኋለሁ::» ይህ ክፍል የሚያመለክተው በእግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት የሚቻለው በሰው ፊት ሊያስደንቁ በሚችሉ አገልግሎቶች ብቻ መጠመድ ሳይሆን ከክርስቶስ ተከታይነት ሕይወት የሚፈልቀውን መንፈሳዊ የሕይወትና የአገልግሎት ፍሬ ሰማየት መስጠት እንደሚገባ ነው::

ዮሐ. 15:1-2 ላይ «እውነተኛው የወይን ግንድ እኔ ነኝ ገበሬውም አባቴ ነው ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል:: ፍሬ የሚያፈራውን ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል» ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ የሚጠብቀውን መልካም የሆነውን የተቀደሰ ሕይወትና ባሕሪን መሆኑን ነው::



- ዮሐ. 15:8 ላይ «ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀመዛሙርት ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል» ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው መሰረቱን በክርስቶስ ያደረገ ማንም ቢሆን ክርስቶስ የሚፈልገውን ሕይወት ከመኖር ሌላ ክርስቶስ የሚጠብቅበትን አገልግሎት እንደሚሰጥ አያጠራጥርም::
- በዮሐ. 15:16 ላይ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመ ረጣችሁኝም አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ» ይላል:: ከዚህ ክፍል የምንማረው ደቀመዛሙርቱን የመረጠው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የአገልግሎት ፍሬ እንዲያፈሩ አቅምና ኃይል የሚሆን እርሱ ክርስቶስ መሆኑን እንዲያውቁ ነው::

ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ያለው ግልጽ ዓላማው የእርሱን እውነተኛ ተከታይነታቸውን መግለጽ የሚችሉት የክርስቶስን ሐሳብና ፈቃድ የተከተለ ሕይወት እንዲኖራቸው ነው:: /ፊል 2:1-11/ ተመልከቱ:: በተጨማሪም የክርስቶስ ዓላማ ያለበትንም አገልግሎት እንዲፈጽሙ መሆኑን መረዳት ይቻላል:: ይኸውም ደቀመዛሙርትን ማፍራት ነው::

## 3ኛ. የክርስቶስ ዓላማ ለቤተክርስቲያኑ በአራቱ ወንጌላትና በሐዋሪያት ስራ እንደተገለጸው:-

የክርስቶስ ዓላማ ለቤተክርስቲያኑ በሚመለከት ስንከታተል በታላቁ የወንጌል ተልዕኮ መሰረት ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠንን የወንጌል አገልግሎት ትዕዛዝ የትኩረት አካባቢንና የአገልግሎት አፈጻጸም በሚመለከት የተሰጠንን መመሪያ እንከታተል::

ሀ. በማቴ. 28:18-20 መሰረት

- የተሰጠን ትዕዛዝ ደቀመዛሙርት አድርጓቸው ነው
- የወንጌል ተልዕኮ ትኩረት አካባቢ ለአሕዛብ ሁሉ ነው
- የወንጌል ተልዕኮ አፈጻጸም መሄድ ማጥመቅና እንዲታዘዙ ማስተማር ነው::

ለ. በማር. 16:15 እና 19:22 መሰረት

- የተሰጠን ትዕዛዝ የምስራቹን ወንጌል ስበኩ ነው::
- የተልዕኮ ትኩረት አካባቢ ወደ አለም ሁሉ መሄድ ነው::
- የወንጌል ተልዕኮ አፈጻጸም ለሁሉ መስበክና በምልክቶች መታጀብ ነው::

ሐ. በሉቃ. 24:6-49 መሰረት

- የተሰጠን ትዕዛዝ በንስሐ ስለሚገኘው ምህረት ማወጅ ነው::
- የተልዕኮ ተግባር አፈጻጸም በአንደበታችን እንድንመሰክር ነው::

ለደቀመዝሙርቱ ክርስቶስ የሰጣቸውን የእርሱ ሐሳብና ፈቃድ

መ. በዩሐ. 13:17-20 መሰረት

- የተሰጠን ትዕዛዝ እኔ እልካችኋለሁ ነው::
- የወንጌል ተልዕኮ ትኩረት አካባቢ በዓለም ሕዝብ ሁሉ መካከል ነው::
- የተልዕኮ አፈጻጸም ክርስቶስ ራሱ አብሮ እየተገኘ የሚፈጸም ነው::

ሠ. በሐዋርያት ሥራ 1:8 መሰረት

- የተሰጠን ትዕዛዝ ምስክሮቼ ናችሁ ነው::
- የትኩረት አካባቢ ኢየሩሳሌም ይሁዳ ሰማሪያና እስከ ምድር ዳርቻ ነው::
- የተልዕኮ አፈጻጸም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ባለማቋረጥ መፈለግ ነው::



ከዚህ በላይ በተመለከትነው መሰረት የክርስቶስ ዓላማ ለራሱ ሕይወት የጠፉትን ሰዎች በመስዋቱ መዋጀት መሆኑንና ለደቀመዛሙርቱ ያለው ዓላማ ከርሱ ጋር በመሆኑን ነው::

ስለሆነም የክርስቶስ ዓላማ ለቤተክርስቲያኑ አንዱ ብቻ ነው ይኸውም በማቴ. 28:18-20 መሰረት ደቀመዛሙርት አድርጉአቸው የሚል ነው::

1ኛ/ በመሄድ:- የትም በተንቀሳቀስን ጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ማብሰር ነው::

2ኛ/ በማጥመቅ:- አዲስ ምዕመን በዓለም ፊት የሚወስደውን አቋምና ክርስቲያኑ ለሞተለት ጌታ ለመሞት መወሰኑን ያመለክታል::

3ኛ/ እንዲታዘዙ በማስተማር:- ኢየሱስ ክርስቶስ ያዘዘውን ሁሉ ባለማቋረጥ ማስተማር የደቀመዝሙር አድራጊዎች ኃላፊነት መሆኑን ያመለክታል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ባዘዘን ታላቁ የወንጌል ተልዕኮ ትዕዛዝ መሰረት የሚከናወንባቸው ሶስት ሂደቶች:-



የጥንት ቤተክርስቲያን ታላቁ የወንጌል ተልዕኮን በሚከተሉት ስልቶች ሊፈጽሙ ቻሉ

1ኛ/ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በዩሐ. 14:16 እና 16:7 መሰረት ከደቀመዛሙርቱ /ከምዕመናን/ የሚኖርና ደቀመዛሙርትን የማፍራት ስራ አብሮ የሚሰራ አጽናኝ እንደሚሰጥ የተስፋ ቃል ሰጥቶታል::

2ኛ/ በሐዋ. 1:4-5 መሰረት ደቀመዛሙርቱ ሌሎችን የክርስቶስ ደቀመዛሙርት በማድረግ ስራ የሚረዳ መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ታዝዘዋል::

3ኛ/ በሐዋ. 1:8 መሰረት ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉ ጊዜ ከኢየሩሳሌም ጀምረው በይሁዳ ሰማሪያ እስከ ምድር ዳርቻ ምስክሮች እንዲሆኑ ታዝዘዋል::

4ኛ/ በሐዋ. 1:14 መሰረት የተባለው መንፈስ ቅዱስ እስኪመጣ ድረስ ለ10 ይሀል ተከታታይ ቀናት በፀሎት ቆይተዋል::

5ኛ/ በሐዋ. 2 መሰረት በዩሐ. 14:16 እና 16:17 በተሰጠው ተስፋ ቃሉ መሰረት መንፈስ ቅዱስ በባለ ሃምሳ ቀን ወረደላቸው:: እነርሱም ታላቁን የወንጌል ተልዕኮ ለማከናወን ተጓዙ::

6ኛ/ በሐዋ. 1:41 መሰረት የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ታላቁን የወንጌል ተልዕኮ በመጀመር በጴጥሮስ የመጀመሪያው የወንጌል ስብከት ሦስት ሺህ ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን በደቀመዛሙርት ላይ ተጨመሩ::

7ኛ/ በሐዋ. 2:42-47 መሰረት ያመኑት ሰዎች

ሀ/ ራሳቸው ለሐዋሪያት ትምህርት በመስጠት የክርስቶስ ተከታይ የመሆን ትምህርት ይማሩ ነበር::



ለ/ የጋራ ህብረት በማድረግ አብረው ያመልኩ ነበር::

ሐ/ እንጀራንም አብረው በመቁረስ ይመገቡ ነበር::

8ኛ/ በሐዋ. 4:4 መሰረት አንዱ ሌላውን በማስተማርና ሌሎችንም እንዲያስተምሩ በማገዛቸው ምክንት ያመኑት ደቀመዛሙርት ቁጥር ጨምሮ አምስት ሺህ ያህል ሆኑ::

9ኛ/ በሐዋ 7 ላይ እስጢፋኖስ በስደት ከተገደለ በኃላ በሐዋ. 8 መሰረት በጣም የከፋ ስደት በደቀመዝሙር አድራጊዎች ላይ ቢነሳም በሮሜ 8:28 መሰረት ጌታ ለክብሩ አደረገውና መስክረውና የተበተኑት ሁሉ የክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል መስክረው የዳኑትን ደቀመዛሙርት ማድረግን አላቋረጡም:: /የሐዋ. 8:1 እና 8:4/

10ኛ/ በሐዋ. 13:1-3 መሰረት የአንጾኪያ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ የወንጌል ማህበረተኛ የሆኑትን በርናባስንና ሳውልን ለወንጌል ስራ ላኩአቸው::

የኤፌሶን ከተማ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭትና ደቀመዛሙርት የማፍራት ሂደት

1ኛ/ የኤፌሶን ከተማ በዛሬ ዘመን ቱርክ በጊዜው በእስያ የታወቀ የወደብና የንግድ መናሃሪያ ከተማ ነበር::

2ኛ/ ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ የወንጌል ስርጭትና ደቀመዛሙርትን የማፍራት አገልግሎት የፈጸመው ከ53-57 ዓ.ም መከከል ማለትም ለ3 ዓመታት ያህል ነበር::

3ኛ/ ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ለመጀመሪያዎቹ 3 ወራት በምኩራብ ወንጌል ካስተማረ በኃላ ተቃውሞ ሲያጋጥመው በጥራኒየስ ት/ቤት በየቀኑ ማስተማር ጀመረ::

4ኛ/ በሐዋ. 19:9 እና 10 መሰረት ጳውሎስ ለ3 ወራት በምኩራብ ባስተማረ ጊዜ አህዛብ በአይሁድ ምኩራብ መግባት ስለማይችሉ ሊያስተምራቸው ዕድል አልነበረም:: ከዚያም ሌላ የሰንበት ቅዳሜ ብቻ ነበር ያስተምር የነበረው ግን ተቃውሞ ከመጣ በኃላ በጥራኒየስ ት/ቤት ለአይሁድና ለአህዛብ ሁሉ የማስተማር ዕድል ተገኘ /ሮሜ 8:28/::

5ኛ/ በሐዋ. 20:21-29 መሰረት ጳውሎስ በምኩራብና በትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ከቤት ለቤት እየተዘዋወረ ያደርግ ነበር::

6ኛ/ ከእስያና ከኤፌሶን ከተማ ስፋት አንጻር ጳውሎስ ብቻውን ወንጌል በእስያ ሁሉ በማብሰር ደቀመዛሙርትን ማፍራት ቀላል አልነበረም ከዚህም ሌላ ጳውሎስ የቆላስያስ ሰዎች ወንጌልን የሰሙት በኤጳፍራ አማካይነት መሆኑን ከመግለጹም ሌላ የቆላስያስን ሰዎችንና የሎዶቂያንም ሰዎች እንዳለየ ነው::

7ኛ/ ከላይ የተመለከተው በእስያና አካባቢው የተሰራጨ የወንጌል ስርጭትና ደቀመዛሙርትን የማፍራት ስራ የተስፋፋው ክርስቶስ ኢየሱስን ባመኑት ደቀመዛሙርት አማካይነት መሆኑን ነው::

በኤፌሶን ቤተክርስቲያን ደቀመዛሙርት የማፍራትን ራዕይ የመጣሉ ውጤት:

1ኛ/ ጳውሎስ ከኤፌሶን በኃላ በመቄዶኒያ አገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ሲሄድ በሚሊጢን ሆኖ የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን አስጠራ::

2ኛ/ በሐዋ. 20:29-31 መሰረት የኤፌሶን ቤ/ክን ሽማግሌዎች የእርሱን ፈለግ የተከተለ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውንና መንጋውን ከተኩላዎች ከሐሰት ትምህርቶች እንዲጠብቁ አስጠነቀቃቸው::



3ኛ/ የኤፌሶን አጥቢያ ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 28:18-20 ያዘዘውን ትዕዛዝ ከመፈጸም ይልቅ በራዕይ 2:1-5 በተለያዩ ጉዳዮች ተጠምዳ እንዳልነበረች ሆና ቀረች አሁንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛም ቤተክርስቲያን የሰጠን ትዕዛዝ «ደቀመዛሙርት አድርጉአቸው» የሚለውም ትዕዛዝ እንድናከብር የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው::




1/ እግዚአብሔርን በግል ማወቅ
2/ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መኖር
3/ ኢየሱስን ለሌሎች መመስከር

4ኛ/ የክርስቶስ ኢየሱስን ትዕዛዝ የምናከብር ቢሆን ደቀመዛሙርት የማድረግ ሂደትን እንደሚከተለው እናደርግ ነበር::

## እግዚአብሔርን በግል ማወቅ

### *የመሪዎች መመሪያ*

እግዚአብሔርን በሙሉ ልብህ በሙሉ ነፍስህ በሙሉ አሳብህ መውደድ በተማርክ ጊዜ ፍቅሩ ውስጥህን (ሕይወትህን) ሞልቶ ወደ ደቀመዝሙርህና ወደ ሌሎች ተርፎ ይፈሳል::

ኢየሱስ በዮሐ.15:5 ላይ እንዲህ አለ:-

*«እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ:: ብዙ ፍሬ የሚያፈራው በእኔ የሚርና እኔም በእርሱ የምኖርበት ነው ምክንያቱም ያለእኔ ምንም ማድረግ አትችሉምና::»*

መንፈሱ በአንተ ውስጥ እንደሚሠራ በማመን በጌታ ላይ በምትደገፍበት ጊዜ እግዚአብሔር በአንተ ሕይወትና ደቀ መዝሙር በምታደርገው ሰው ሕይወት እንደሚሠራ ድፍረት ሊሰማህ ይችላል::

## ከደቀመዝሙርህ ጋር ቀጠሮ እንዴት መያዝ ይቻላል?

* ክርስቶስን አሁን ከተቀበለው አዲስ አማኝ ጋር ክርስቶስን በመቀበል የአንተን ልምምድና እንዴት እድገት እንዳሳየህ በጥቂቱ አካፍለው::
እንዲህ በማለት ሰውየውን ለመገናኘት ፈቃደኝነትህን ግለጽ::

«ከክርስቶስ ጋር ባለህ ግንኙነት ለማደግ የሚ ረዱህን አንዳንድ ነገሮች አብሮ ለማየት በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደገና መገናኘት እንችል ይሆን?»



መልሱ አዎን ከሆነ አንድ ተስማሚ ጊዜና ቦታ ወስን:: መልሱ የለም ከሆነ ሰውየው ወደ ቤተ ክርስቲያን ወይም ክርስቲያኖች ተሳትፎ በሚያደርጉበት ሌላ ተግባር ላይ ጋብዘው::

* ለጥቂት ጊዜ ክርስቲያን ከሆነው ሰው ጋር
ደቀ መዝሙር ማድረግ ለአንተ ምን ትርጉም እንደሚሰጥህና በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሰዎች ደቀ መዝሙር አድራጊዎች እንዲሆኑ ስለማስፈለጉ ጉዳይ አሳብህን አካፍለው::
ደቀ መዝሙር በማፍራት ያለውን እስቸጋሪ ሁኔታ አካፍለው::
2ኛ ጢሞ.2:2 አንብቡ::
ፈቃደኝነቱን አግኝ:: ከዚያም የምትገናኙበትን ጊዜና ቦታ ወስኑ::

## ጥሩ የሆነ ግንኙነት እንዴት ማፍራት ይቻላል?

1. በየጊዜው ለደቀመዝሙርህ ለመጸለይ ታማኝ ሁን (ፊልጵ.1:3-6)
2. እውነተኛ ፍቅርና የግል ፍላጎት እንዳለህ ግለጽ::በትኩረት አዳምጥ::ሰውየው ለአንተ ጠቃሚ እንደሆነ ሊሰማውና አንተም ራስህን እንዳዘጋጀህለት ሊያውቅ ይገባል::
ስለዚህ ሰው ትክክለኛ ሸክምና ግንዛቤ ይኑርህ:: «ነገሮች እንዴት እየሄዱ ናቸው» ብለህ ጠይቅ:: ስለ ሰውየው የሚኖርህ ሸክም የጥናት ክፍሉን ከማየት በላይ ጠቃሚ ነው:: ሰዎች የቱን ያህል ስለእርሱ እንደሚገድህ ካላወቁ

በስተቀር የቱንም ያህል እውቀት እንዳለህ ማወቁ ደስታ አይሰጣቸውም::

4. ሁሉታችሁም ደስ የሚያሰኛችሁን ነገር አብሮ በማድረግ ጓደኝነታችሁን ለመገንባት ሞክሩ:: ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ለመሆን ÷ በአምልኮ ሥርዓት÷በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በማኅበራዊ ነክ ጉዳዮች. . . ወዘተ ላይ ለመገኘ ት ጋብዘው::
5. የራስህን ሕይወትና መልእክቶች አካፍለው (1ኛተሰ.2:7-8)::
    - የመልካም ጸባይ ምሳሌ ሁን (4:9)::
    - የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት እንዴት በሕይወትህ ለመተርጎም እየተማርክ እንዳለህ ግልጽ አድርግ::
    - አብራችሁ በምትሆኑበት ጊዜ ሸክማችሁን ለእግዚአብሔር በማቅረብ ረገድ እራሳችሁን ሁኑ::
    - በደቀ መዝሙርህ በታየው ማናቸውም አዲስ ግንኙነት በአድናቆት ምላሽ ስጥ:: ድሮው የማውቀው ነገር ነው በማለት ፍላጎቱን ላለመግደል ጥንቃቄ አድርግ::

እነዚህን ነገሮች አስታውስ

- ግለሰቡን ከምግባር አንፃር ሳይሆም በፍቅርና በእምነት መሠረት ላይ ተቀበለው::
- የዓይን ግኙንትን ጠብቅ÷ፈገግ በል÷ እንደዚሁም ለውየውን በስሙ ጥራው::
- በጥያቄ ወይም በመልስ ላይ ከቶ አትሳቅ::



- በማንኛውም ሌላ ሰው÷ቡድን÷ወይም ድርጅት የአሉታዊ ባሕርይ ከቶ አታሳይ::
- የደቀ መዝሙርነትን ሥራ ከማስተማር ይልቅ በማካፈል ደረጃ ውሰደው ፊልጵ.2:3 4:ቆላ.4:6::ለቀረበው ጥያቄ መልስ በማይርህ ጊዜ በጸጋ ተቀበል:: አብራችሁ ተመልከቱ ወይም መልሱን ራስህ ፈልግ:: ከዚያ በኃላ ወደ ተጠቃሹ ተ መለስ::

## የክትትል ክፍለ ጊዜያትን እንዴት መምራት እደሚገባ

ከመገናኘታችሁ በፊት ለእያንዳንዱ ትምህርት የተዘጋጀውን የትምህርት እቅድ በማጥናት ራስህን አዘጋጅ :: ጠቃሚ ምክር÷ በራስህ የትምህርት ወረቀቶች ላይ ቁልፍ የመሸጋገሪያና የመወያያ ጥያቄ ጻፍ::

1. ግኙኝነት መሥርት::ትምህርቱን ለማስተማር ቢያንስ 90-120 ደቂቃ ተጠቀም::
2. የተሰጠውን የመረጃ ጥቅሶች ጮክ ብለህ ለማንበብ ተ ራ ወስድ::ጊዜ ከፈቀደ ወይም በዚያ ነጥብ ላይ ግለሰቡ ጥያቄ ካነሣ ብቻ በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች ተመልከት::
3. በትምህርቱ ላይ ባሉት እያንዳንዱ ነጥብ ላይ በምትወያዩበት ጊዜ ደቀ መዝሙርህ ግልጽ ስላልሆነለት ማናቸውም ነገር ጥያቄ እንዲጠይቅህ አደፋፍረው:: ውይይት የሚያስነሡና መረዳትን የሚያስገኙ ሌሎች ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው::

* ያ አሳብ ጠቃሚ እንደሆነ ለምን አሰብህ?
* ያንን አሳብ ከጓደኞቹህ ለአንዱ እንዴት አድርገህ ትገልጸዋለህ?
* ያ ጥቅስ ሌላ ምን አሳቦችን ይፈጥራል?
* የዚያ ጥቅስ እውነት እንዴት አድርጎ በሕይወትህ ለውጥ ማምጣት (ማስገኘት) ይችላል?

4. በየትምህርቱ 4ኛው ነጥብ 4 በእያንዳንዱ ወረቀት ላይ ግለሰቡ በሳምንቱ ውስጥ ወደሚያከናውኑት የግል ሥራ ያመራል :: እነዚህ እንደ «የቤት ሥራ» እንዳይታዩ ጥንቀቄ አድርግ:: በጣም አስደሳች የሆኑ በትምህርቱ ውስጥ የተገኙትን አሳቦች የሚያጠናክሩ አጫጭር ተግባሮች ናቸው::



# እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ

## የማይቋረጥ የጽሞና ጊዜ እንዴት ሊረኝ ይችላል?

መለመን: ዓይኖቼን ክፈት: ከሕግህም ተአምራትህን አያለሁ:: መዝ. (119):18

ማመስገን: «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል»::2ጢሞ.3:16-17

ትምህርት: ስለ እግዚአብሔር ስለራሴ እና ስለሌሎች ላውቅ የሚገባኝ ነገር ምንድር ነው?

ተግሣጽ: ላምንና ላደርግ የማይገባኝ ነገር ምንድር ነው?

መታረም:በአሳቦቼ በአመለካከቴ ወይም ፈቃዱን በመታዘዝ: ላደርገው የሚገባኝ ነገር ምንድን ነው?

መለማመድ ያለብኝ: ነገር የእግዚአብሔር ቃል ወይም ፈቃዱን በመታዘዝ ላደርገው የሚገባኝ ነገር ምንድን ነው?

- ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ላውቅ: ልተው ልለወጥ ወይም ላደርግ የሚገባኝ ነገሮች እስከሚያሳዩኝ መጠበቅ::

## በዕቅድ መመራት

1. የማነበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መምረጥ
2. እግዚአብሔር በግል የሚናገረኝን ጥቅስ እስከሚያሳየኝ ድረስ ማንበብ
3. በማስታወሻ ደብተሬ የምጽፋቸው፡
   ሀ. እግዚአብሔር በግል የተናገረኝን ጥቅስ መርጦ መፃፍ?
   ለ. እግዚአብሔር በዚህ ጥቅስ የተናገረኝ ለምንድነው?
   (እግዚአብሔር ምንን እንዳውቅ እንድተው እንድለወጥ ወይም እንዳደርግ እንደሚፈልግ መጻፍ
4. ስለሚያስተምረኝ ነገር እግዚአብሔርን ላመሰግን ይገባኛል እንዲሁም እንዲረዳኝ መለመን፡፡
5. እግዚአብሔር በግል የተናገረኝን ጥቅስ 3 በ5 በሆነ ካርድ ላይ መጻፍ፡፡
6. እግዚአብሔር የተናገረኝን ጥቅስ ቀኑን ሙሉ ማሰላሰል፡፡
7. ወደ መኝታ ከመሄዴ በፊት እግዚአብሔር የተናገረኝ ጥቅስ ማሰላሰል

## ከላይ ለተገለጸው እቅድ የአፈጻጸም መመሪያ

1. ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል መምረጥ

   ሀ. ከወንጌላት በአንዱ ማለትም በዮሐንስ ወንጌል ወይም

   ለ. ከአጫጭር መልዕክቶች አንዱን ማለትም ኤፌሶን ወይም ያዕቆብ ወይም

   ሐ. መጽሐፈ ምሳሌ ወይም መዝሙረ ዳዊትን መጀመር አለብኝ፡፡

2. በግሌ የሚናገረኝን ጥቅስ እስከሚያሳየኝ ማንበቤን መቀጠል፡፡ ምናልባት በጥቂት ጥቅሶች የሚናገረኝን አገኝ ይሆናል፡፡

3. በማስታወሻ ደብተሬ የምጽፍቸው፡

   ሀ. እግዚአብሔር የተናገረኝን ጥቅስ፡፡

   ለ. እግዚአብሔር በዚህ ጥቅስ ለምን እንደ ተናገረኝ



በዚህ ጥቅስ መሠረት ላውቅ ልተው ልለወጥና ላደርግ የሚገባኝን እግዚአብሔር እንዲያሳየኝ መፀለይ

4. በዚህ ጥቅስ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለብኝ ነገሮች

   ሀ. ስለ እግዚአብሔር ባህርይ የተገለጠልኝን በማስመልከት

   ለ. የማስጠኝን የተስፋ ቃሎችን በማስመልከት

   ሐ. ለትዳር ጉደኛዬ፣ ለልጆቼ ፣ለወላጆቼ ለሥራ ባልደረቦቼ ወዘተ (የሚናገረውንና የሚሰጠውን ተስፋ በተመለከተ ጊዜ የሚረዳኝ ከሆነ በማስታወሻ መጻፍ አለብኝ)፡፡

5. 3በ5 በሆነ ካርድ እግዚአብሔር ያስተማረኝን ነገር መጻፍ አለብኝ ጥቅሱን በዐረፍተ ነገር መልክ በመጻፍ ለማንበብ እንደሚስብ ማዘጋጀት፡ እግዚአብሔር ለልቤ ለይቶ የማያሳየኝን ቁልፍ ቃላትንና ሐረግን ከሥሩ ማስመር

6. በተራ ቁጥር 4 መሠረት እግዚአብሔር ስለተናገረኝ ነገርና ስለገለጸልኝ እውነቶች ቀንኑ ሙሉ ማሰላሰል፡፡

7. እግዚአብሔር አእምሮዬን ለማደስ ልጠቀምበት ስለሚችል ከመተኛቴ በፊት እግዚአብሔር በቀኑ መጀመሪያ ያሳየኝን ጥቅስ ለመጨረሻ ጊዜ መሰላሰል፡፡

# እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ

## ትምህርት 1. ከእግዚአብሔር ጋር መጀመር

> «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው»
> 2ኛ ቆሮ. 5:17

> የዓለማት ሁሉ ጌታ ከሆነው ታላቁ እግዚአብሔር ጋር የግል ግኑኝነት ከመመሥረት የበለጠ የሚያስደስት ነገር እንዳለ ለማሰብ ሞክረህ ይሆን? ኢየሱስ ክርስቶስን በሕይወት ማወቅ ከእግዚአብሔር ጋር አስደናቂውን ሕይወት የመለማመድ ጅማሬ ነው::ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበልክ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተማምን ግንኙኝነት እንዳለህ በእርግጠኝነት ማወቅ የምትችለው እንዴት ነው?

### 1. ከኢየሱስ ጋር ባለህ ግንኙነት የተመሠረተ እምነት

ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለህ አዲስ ግኑኝነት ድፍረት ሊሰማህ ይችላል:: ምክንያቱም ክርስቶስን በተቀበልክ ጊዜ እግዚአብሔር በፍጹም ይቅር ስላለህ ነው:: ተ ቀብሎሃልም::ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ አማካኝነት ይህንን ግኑኝነት ለመመሥረት ብቁ ያደረጉን የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ብቻ ናቸው::

> በኤፌ. 2:8-9 ባሉት 3 ጠቃሚ ቃላት ላይ ትኩረት አድርግ ምክንያቱም እናንተ የዳናችሁት በእምነት አማካኝነት በጸጋው ነው ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ በእናንተ ሥራ የተገኘ አይደለም:: ማንም ሰው እንዳይመካ ይህ የመዳን ጸጋ የተገኘው ከሥራ አይደለም::

ጸጋ:- ጸጋ ማለት ከእግዚአብሔር የሆነልን የማይገባን የውዴታ ስጦታ ነው ከእግዚአብሔር ጋር ግኑኝነት የተፈጠረልህ በምን መሠረት ነው?(አንደኛውን መልስ ክበበው)

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ግኑኝነት ሊኖረኝ ተገቢ ነው::

ለ. ጥሩ ነገሮችን ስላከናወንኩ መብቱ ተሰጥቶኛል



ሐ. እኔ የቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ::

መ. ክርስቶስ ወደ ሕይወቴ በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔርን የደህንነት ነፃ ስጦታ ተቀበልኩኝ::

ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ ግኑኝነት የሚገባኝ አልነበረም በየትኛውም የራሴ ጥሩ ምግባር አላገኘሁትም:: በሕይወቴ ያከናወንኩት የየተኛውም የሥራ ውጤት ሳይሆን የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ነው::

<u>የዳነ:-</u> ማለት የተረፈ፣ ከፍርድ ነፃ የወጣ ማለት ነው::

ሮሜ 6÷23ን አንብቡ

እንደ ሮሜ 6:23 የመጀመሪያ ግማሽ ሃሳብ የኃጢአት የመጨረሻ ውጤት ምንድነው? (ተወያዩበት)

"የኃጢአት ደመወዝ__________ ነው

ከምንድነው የዳናችሁት (የተረፋችሁት)? (ትክክለኛ መልሶችን ክበብ)

ሀ. ሥጋዊ ሞት ለ. መንፈሳዊ ሞት ሐ. ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት የሮሜ 6:23 ሁለተኛው ግማሽ ሃሳብ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ያስታውሰናል::

« ከእግዚአብሔር የሚሰጠው _______ግን በጌታችን በኢየሱስ አማካኝነት የሚገኘው የዘላለም ሕይወት ነው::»

<u>አስታውስ:</u> መጽሐፍ ቅዱስ የዘላለም ሕይወት ለእኛ ከእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ እንጂ የሥራ ውጤት አለመሆኑን ያረጋግጥልናል::

<u>እምነት</u>:-· እምነት ማለት ማመን ፣ መታመን ፣የአእምሮ የዝንባሌና የድርጊት መሠጠት ማለት ነው:: እምነት እግዚአብሔርን ማመን ወይም በርሱ

መታመን እንደዚሁም በቃሉ መታመን ነው::

1. ክርስቶስን በተቀበልክበት ጊዜ የእግዚአብሔርን የውዴታ ተቀባይነት ለማግኘት:-በራስህ ችሎታ ታምነሃልን?አዎን/ አይደለም::
2. ያድንህ ዘንድ እምነትህን በቤተ ክርስቲያን ላይ አድርገሃል?አዎን/ አይደለም
3. እምነትህን በደንቦች ስብስብ ላይ አድርገህ ይሆንን? አዎን/አይደለም::
4. እንደ ጌታና አዳኝህ እምነትህን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አድርገሃልን?አዎን/አይደለም

ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግኑኝነት ዘላለማዊና አስተማማኝ ነው ምክንያቱም እምነትህን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ በፈጸመው ሞትና ትንሣኤው ላይ አድርገሃልና::

ክርስቶስ ለአንተ ባደረገልህ ነገር በታመንህ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀሃል ዘላለማዊ ግንኙነትህንም መስርተሃል::

- በሕይወትህ በእርግጥ የእግዚአብሔር በመሆንህ ምክንያት ዛሬ የምትሞት ብትሆን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደምትሔድ ማወቅ ወደምትችልበት ደረጃ ደርሰሃል ወይ?
- ለምሳሌ ዛሬ በዚህ ሰዓት በእግዚአብሔር ፊት የምትቆም ቢሆንና ወደ መንግሥተ ሰማይ እንድትገባ የፈቀድኩልህ ለምንድነው? ብሎ ቢጠይቅህ ምን ማለት ትችል ይሆን?» (መልስህን ለደቀመዝሙር አድራጊህ ስጥ)



## 2. ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስላለህ ግንኙነት መሠረታዊ እውነቶች የመረዳት አስፈላጊነት

ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለህ ግኑኝነት እውነት የሆኑ ብዙ የሚያስደስቱ ነገሮች አሉ:: የሚከተሉትን እውነቶች መረዳትህ በክርስቶስ ማን እንደሆንህ ለማየትና ማደግ የምትችልበትን የጸና መሠረት ለመገንባት ይረዳሃል::

| | |
|---|---|
| 1. ክርስቶስ ኃጢአቴን በሙሉ ይቅር ብሎልኛል | 1. ዕብ.10:12-14 ያለውን ክፍል አንብብ:: ለኃጢአትህ ይቅርታ ክርስቶስን ባመንህ ጊዜ የፊቱ ያሁኑና የወደፊቱ ኃጢአትህ በሙሉ ይቅር ተብሎልሃል:: ኃጢአትህ በሙሉ ይቅር መባሉን ማወቅ ላንተ ምን ልዩነት ያመጣል (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ) |
| 2. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አደረገኝ | 2. ዮሐ.1:12-13ን አንብብ::ስምህን በባዶዎቹ ቦታዎች ጻፍ:: «እርሱን ለተቀበሉት ለ በስሙ ና ለሚያምኑ ለ--------------------የእግዚአብሔር ልጅ ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው::» ገጽ 53ን አንብብ |
| 3. ክርስቶስ ወደ ሕይወቴ መጣ ከቶም አይተወኝም | 3. ገላ.2:20ን አንብብ ይህ ክፍል ከክርስቶስ ጋር ያለህ አዲስ ግኑኝነት ስዕላዊ መግለጫ ነው:: ካንተ ጋር ባለው ግኑኝነት ክርስቶስ በአሁኑ ጊዜ የት ይገኛል? (ተወያዩበት) ዕብ. 13:5ና ዮሐ.6:37ን አንብብ::በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው ክርስቶስ ሊተውህ የሚችለው?በዚህ አስተያየት ክርስቶስን መቀበል የሚገባን ለምን ያህል ጊዜ ነው:: (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ) |
| 4. ክርስቶስ አዲስ ሕይወት ሰጠኝ | 4. 2ኛ ቆሮ. 5:17ን አንብብ:: የግል አዳኝህና ጌታህ እንዲሆን ክርስቶስን ባመንህ ጊዜ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ጀምረሃል::ከእርሱ ጋር ባለህ ግንኙነት ባደግህ ጊዜ እግዚአብሔር ባንተ ውስጥ በርካታ አዲስ ባሕርያት እንድገቱን በጠበቀ ሁኔታ ያፈራልሃል:: |

| | |
|---|---|
| 5. ክርስቶስ የዘላለም ሕይወት ሰጠኝ | 5. ዮሐ .17:3ን አንብብ: ምንድነው? የዘላለም ሕይወት ክርስቶስን በተቀበልን ጊዜ የሚጀምር ግኑኙነት ነው:: 1ዮሐ.5:11-13 አንብብ::የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በማን ነው? በዘላለም ሕይወት ምን ይገኛል?የዘላለም ሕይወት አለህ? የዘላለም ሕይወት የጀመረው መቼ ነው? |

ዛሬ ማታ የምትሞት ቢሆን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር እንደምትኖር የቱን ያህል እርግጠኛ ነህ ?

ማጠቃለያ:- እነዚህ እውነቶች በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚመሠረቱ ናቸው እንድም ሰው ካለ ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን እውነቶች መቀበል አይችልም:: በኢየሱስ ክርስቶስ ባመንክ ጊዜ ወዲያውኑ አድራሻህ ይለወጥና የእግዚአብሔር ቤተሰብ ትሆናለህ::

የግል ሕይወት ምስክርነት

- መቼ እና የት ነው ክርስቶስን የተቀበልከው?
- ክርስቶስን በማመንህ ያገኘኸው የሕይወት ለውጥ ምንድነው?
- ከክርስቶስ ጋራ ሕብረት የሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዳሉ ታውቃለህ?

3. <u>ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለህ ግንኙነት ጥርጣሬዎችን ማስወገድ የሚቻለው እንዴት ነው?</u>

ምንም እንኳን <u>ስሜት</u> ጠቃሚነት ያለው ቢሆንም ከክርስቶስ ጋር ያለህ ግንኙነት በየቀኑ ሊለዋወጥ በሚችሉ ስሜቶች ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር እውነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ዮሐ.17÷17 እና ሮሜ 1÷17ን አንብብ:: ጥርጣሬዎች÷ጥያቄዎችና የተለያዩ የስሜት ዓይነቶች በማናቸውም የሰው ዘር



ዘንድ የተለመዱ ናቸው:: ነገር ግን ማንም ከክርስቶስ ጋር ባለው ግኑኝነት የማያስተማምኑ ዓይነት መሰኪያዎች ናቸው ክርስቲያን በሚያስተማምነው በእግዚአብሔርና በቃሉ በእምነት ይኖራል ::

የዚህ ባቡር ስዕላዊ አገላለጽ በእውነት (በእግዚአብሔርና ቃሉ) በእምነት(በእግዚአብሔርና በቃሉ ባለህ መደገፍ) እንደዚሁም <u>በስሜት</u> መካከል ያለውን ግንኙነት ምሳሌ ያስረዳል::




ባቡሩ በተጎታች ወይም ያለተጎታች ሊንቀሳቀስ ይችላል:: ሆኖም ባቡሩን በተጎታች መሳብ ውጤት የሌለው ሙከራ ነው::በተመሳሳይ ሁኔታ በስሜቶች ላይ አትደገፍ::የሥልጣንህ ምንጭ የእግዚአብሔር ቃል ተስፋዎች እንጂ ስሜቶች መሆን የለባቸውም:: ለምሳሌ በነገው ዕለት ከእንቅልፍህ ብትነቃና እግዚአብሔር በአጠገብህ እንደሌለ ቢሰማህ ምን ትሆናለህ? እግዚአብሔር የት ነው ያለው? ለምን? እምነትህን በርሱ በእግዚአብሔር ታማኝነትና በሚያስተማምነው ቃሉ ላይ አኑር:: ስለ ቃሉ ይበልጥ በተማርክና በተረዳህ መጠን ጥርጣሬዎችህን ይበልጥ ጠንካራ በሆኑ እምነቶች መመለስ ያስችልሃል::ስሜቶችህ ላለህበት ሁኔታ ሳይሆን እግዚአብሔር ቃል እውነት ምላሽ መስጠት ይጀምራሉ::

### 4. ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለህ ግንኙነት ማደግ

ክርስቶስ ለኃጢአትህ ሁሉ ባደረገው ክፍያ በማመንህ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን የግንኙነት መሠረት በመረዳትህ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለህ ግንኙነት አንዳንድ እውነቶችን ማየት ስለቻልህ ከክርስቶስ ጋር በሚኖርህ ግንኙነት ድፍረት ሊሰማህ ይገባል፡፡

በዚህ ሳምንት ሁለተኛውን ትምህርት ከመጀመርህ በፊት በክርስቶስ እያደግህ ባለህበት ጊዜ እነዚህን እውነቶች የሕይወትህ ክፍል ማድረግ ጀምር፡፡ ማንኛቸውንም ጥርጣሬ ዎች በእግዚአብሔር ቃል እውነት መመለስ ይቻልህ ዘንድ እነዚህን ቁልፍ የደህንነት ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ጻፍ፡፡

- ☞ እኔ ይቅር ተብያለሁ ቆላ.1÷13-14 2÷13
- ☞ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ዮሐ. 1÷12 ሮሜ 8÷15 1ዮሐ.3÷1
- ☞ ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ይራል ራዕ.3÷20 ገላ.2÷20
- ☞ እኔ አዲስ ሕይወት አለኝ ዮሐ. 5÷17፣ ኤፌ. 2:4-5
- ☞ እኔ የዘላለም ሕይወት አለኝ 1ዮሐ 5:11-13፣ ዮሐ. 5:24 10:27-29

እግዚአብሔር ይመስገን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ እውነቶች አሁን ስለ አንተ እውነት ናቸው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ እውነቶች ማወቅ በክርስቶስ ላለህ እድገት ወሳኝ ነው፡

በእያንዳንዱ ቀን ሰማያዊ አባትህን ስለማንነቱ እያወደስከው በሕይወትህ ስላደረገውና እያደረገልህ ስላለው እያመሰገንህ



የምታሳልፍበት ጊዜ ይኑርህ፡፡ ቃሉ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን እያነበብህ እርሱን በማዳመጥ በጸሎት ከእርሱ ጋር እየተነጋገርህ ሕብረት ማድረግህን ቀጥል፡፡

በዚህ ሳምንት መቼና እንዴት ክርስቶስን እንደተቀበልህ ለአንድ ሰው መስክር፡፡ ክርስቶስን ከተቀበልህ በኃላ የተ ለማመድከውንም ለውጥ ንገራቸው፡፡

> ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜና እግዚአብሔር እንድንሆን ከፈለገን ነገር ስንጎድል ምን ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ ትምህርት ሁለትን ተከታተል፡፡

ጊዜህ አዳዲስ ጥቅሶችን ለመፈለግ ጊዜ በማይኖሩህ በማንኛ ውም ቀን ለምስጋናና በቃል ጥናት መጠቀሚያ ለማድረግ በቀላሉ ለማግኘት እንዲቻል በተገቢ ሥፍራ አኑር::

☞ ክርስቶስን እንዴት እንደተቀበልህ እና ሕይወትህን ለክርስቶስ ካስረከብህ በኋላ በሕይወትህ የታየውን ለውጥ ጻፍ:: ምስክርነትህንም ለማሳጠር 3በ5 በሆነ ካርድ ክርስቶስን ከመቀበልህና ከተቀበልህ በኋላ ሕይወትህን ለመግለጽ ጥቂት ገላጭ ቃሎችን ዘርዝር :: ለምሳሌ አስቀድሞ መቆጣት መጠራጠር ግራ መጋባት ክርስቶስን ከተቀበልህ በኋላ ይቅር መባል ሰላም የበለጠ መተማመን . . . ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ::

☞ የምሥክርነቴ ናሙና:- ከእናቴ ከተለየሁ በኋላ አለመረጋጋትና መቆጣት ያስቸግረኝ ነበር:: አንድ ቀን ኢየሱስ ወደ ሕይወት መምጣት እንደሚፈልግ መቆጣቴን ይቅር እንደምለኝና ጨርሶ እንደማይተወኝ ተረዳሁኝ እኔም « ጌታ ኢየሱስ ወደ ልቤ ግባ ኃጢአቶቼን ይቅር በለኝ ና አንተ የምትፈልገው ሰው አድርገኝ » ብዬ ፀለይኩ ሕይወቴን ለክርስቶስ ካስረከብኩኝ ጊዜ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ይቅር እንደተባልኩኝና ኢየሱስም ጨርሶ እንደማይተወኝ በመረዳቴ ሰላምና መረጋጋት በሕይወቴ ሰፈነ::

☞ ያዘጋጀኸውን ምሥክርነት እስከ አሁን ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች ለመመሥከር ካልተዘጋጀህ ለጥቂት ክርስቲያን ጓደኞችህ (ደቀ መዘሙር ጓደኛህ በተጨማሪ) አካፍላቸው:: ለክርስቲያን ጓደኞችህ ማካፈል ካልተለማመድህ ክርስቲያን ላልሆኑ ምስክርነት ለማካፈል ድፍረት አታገኝም:: በነዚህ የደቀመዝሙርነት መግቢያ ትምህርቶች አመካይነት 3ኛ ሰው ካስተማርክ በኋላ አማኝ ላልሆኑ ሰዎች ምስክርነት ለማካፈል በቀላሉ ድፍረት ታገኛለህ::



☞ በንግግርህ ወቅት ገላጭ ቃሎችን ተጠቀምባቸው የምትመሰክርላቸው እና ደቀመዝሙር የምታደርጋቸው ሰዎች ኢየሱስ በሕይወትህ ያደረገውን ለውጥ ለመስማት የሚፈልጉ ናቸው::2ቆሮ 1:3-4 «የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ:: እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት ሁሉ ሌሎችን ማጽናናት እንችላለን»::

ምስክርነትህን ለሌሎች ለማካፈል እንድትችል በር እንዲከፈትልህ ፀልይ:: እግዚአብሔርን በሕይወት ካወኩኝ ጀምሮ በሕይወቴ የተለማመድኩዋቸውን ለውጦችን ላንተ ማካፈል እችላለሁን በማለት የራስህን ታሪክ ለማካፈል በፈለክ ቁጥር ፈቃድ ጠይቃቸው::

መልሱ አዎን ከሆነ የሕይወትህ ለውጥ ምሥክርነት ከ3-5 ዐረፍተ ነገር በማሳጠር አካፍል:: ምሥክርነትህን ሰሚ ዎቹ በስፋት ለመስማት ዝግጁ ካልሆኑ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁህ አስቀድመህ አበረታታቸው:: መልሱ አይሆንም ከሆነ ለእነርሱ ፈቃደኛ መሆንህን አሳውቃቸው:: አሁን እነርሱ አይሆንም ሲሉ መቀበል እነርሱ ፈቃደኞች ሲሆኑ ወደእነርሱ ቀርበህ ለመመስከር ይረዳህ ይሆናል:: እስከዚያው እግዚአብሔር ሰላምና መረጋጋት ማግኘት ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ እንደሚገኝ እንዲያሳያቸው ፀልይላቸው:: ወይም የመረጥከውን ሌላ የወንጌል ምስክርነት በራሪ ጽሑፍ ከክርስቲያን ጓደኞችህ ጋር ከተለማመድክ አማኞች ካልሆኑ ሌሎች ጋር በድፍረት ማካፈል ትችላለህ::

እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ ትፈልጋለህ? የሚለውን በራሪ ጽሑፍ ለማየት ዝግጁ ለሚሆኑት ሁልጊዜ የወንጌል በራሪ ጽሑፎችን በመጠቀም እነዚህ በራሪ ጽሑፎች እግዚአብሔር በሕይወት ማወቅ እንድትችል ያስረዱሃል በማለት በዝግጅት ቅ ረባቸው:: ከበራሪው ጽሑፍ ስለተረዳኸው ያለህን ሃሳብ እባክህ ልወቀው በላቸው::ከዚያም ለወንጌል መመስከሪያ በራሪ ጽሑፍ ምላሻቸው ምን እንደሆነ ለመረዳት እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ ትችላለህ::

ስለበራሪው ጽሑፍ ምን ታስባለህ ? ለአንተ ምን ትርጉም ይሰጠሃል?

አስደናቂውን እግዚአብሔርን በሕይወት የማወቅ ግንዛቤ አገኘህ ወይ?

ደቀመዝሙር የምታደርገውንም ሰው ትምህርት አንድን በሕይወትና በአገልግሎት ለመተርጎም ለእርሱ/ ለእርሷ ኃላፊነት ስጠው/ስጣት::

<u>አስታውሰ</u> - ለራስህ የማታደርጋቸውን ነገሮች ደቀመዝሙሮችህ እንዲያደርጉ ኃላፊነት አትስጣቸው::



# እግዚአብሔርን በግል ማወቅ

## <u>*የመሪዎች መመሪያ*</u>

**1. ከእግዚአብሔር ጋር መጀመር**

**የክፍለ ጊዜው ትኩረት**

በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ባንተ እምነት ምክንያት ከእግአዚአብሔር ጋር ስላለህ ግንኙነት ኩራት ሊሰማህ ይገባል:: ከዚህ ግንኙነት የተነሳ እግዚአብሔር ብዙ ቃል ኪዳን ገብቶአል::

ዝግጅት:

አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ፣የትምህርት ወረቀት 2 እና የወንጌል ትራክት ይዘህ ና:: የጽሞና ጊዜውን ወረቀት የሚጠቀም ከሆነ የ3በ5 ካርድ ይዘህ ና:: (አራቱ ትምህርቶች ከጥሞና ጊዜው ወ ረቀት ጋር በፓኬት ውስጥ ይገኛሉ:: እነዚህም የወንጌል ትራክት ፣ የመንፈስ ቅዱስ ትራክት ፣ የመሪው መመሪያና « በክርስቶስ እኔ ማንነኝ » የሚል አነስተኛ ጥራዝ ናቸው::) በትምህርቱ ውስጥ በአነስተኛ ፊደል የተጻፉትን ጥቅሶች ከልሳቸው ::

ግንኙነት መስርት:-

« በአንተ በኩል ነገሮች እንዴት እየተካሄዱ ናቸው » ብለህ ጠይቅ:: ጥቂት ደቂቃዎች በመውሰድ በሳምንት ውስጥ ስለተካሄዱት ጉዳዮች ሐሳብ ለሐሳብ ተለዋወጡ::

ወደ ርእሱ ሽግግር:-

ከአንተ ጋር ለመሆን ከልቤ ተስፋ አደርግ ነበር:: ከእግዚአብሔር ቃል አብሮ መማር ታላቅ ነገር ነው:፤

የትምህርቱን ወረቀት በመጠቀም:-

በተመሳሳይ ጊዜ በተመሳሳይ ነገር ላይ ሁለታችንም እንድናስብ

በማድረጉ ይህንን ወረቀት ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ::
መረጃውን ጮክ ብሎ ለማንበብ ተራ እንወስዳለን::

1--------የኤፌ2:8-9 አሳብን በተመለከተ ክፍሉን በሙሉ አንብብ ያለአንተ እርዳታ ግለሰቡ ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲሰጥ ዕድል ስጠው::ይህ አሰራር ነገሮችን የመረዳት ነገር ካለ ያስታውቅሃል::መልሱ ትክክል ካልሆነ ወደ ጥቅሶቹ እንደገና በመሄድ መልሶቹ ሳይገለጹ ወደ ትክክለኛው መደምደሚያ ሐሳብ እንዲመጡ እርዳቸው::አላማው ግለሰቡ ደህንነት ከስራ ሳይሆን ከእምነት መሆኑን ተረድቶት እንደሆነ ለማረጋገጥ ነው::

2. ----- ደቀመዝሙርህ ዓረፍተ ነገሮቹንና ጥቅሶቹን በሙሉ አንብቧል ወይ ? ትኩረትህን በጥያቄዎቹ ላይ አድርግ::

ዕብ. 10:12-14 (ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ግንኙነት መታመን፣ሠላም)

ዮሐ.1:12-13 (ቁጥር 13 በትውልድ ወይም በራስ ጥረት አይደለም)

ገላ.2:20 (በስም ብቻ መኖር )

ዕብ.13:5፣ዮሐ.6:37 (ሁኔታዎች አይደለም፣አንዴ ብቻ)

ዮሐ.17:3 (እግዚአብሔርንና ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ

1ዩሐ.5:11-13 (የዘላለም ሕይወት በልጁ ነው፣ በሕይወታቸው ኢየሱስ ያላቸው ሁሉ በተቀበሉት ጊዜ የጀመረ ዘላለም ሕይወት አላቸው::)

ሰውየው መቶ በመቶ ካልመለሰ ለምን ብለህ ጠይቅ::



ባለፈው ኃጢአት ላይ በመመስረት ይቅር እንደማይባል ጥርጣሬ ካለው/ካላት ቆላ.2:13-14 አመልክታቸው::ኢየሱስ ለጥቂት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ኃጢአታችን ዋጋ ከፍሏል:: እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት እንጂ ተስፋ ብቻ እንዳላገኘን ተናግሯል (1ዮሐ.5:13)::

የግል ምስክርነት ጥያቄዎችን አንሳ:: ክርስቶስ በሕይወቱ ወይም በሕይወቷ ስላመጣው ለውጥ ለሌሎች እንዲናገር ደቀመዝሙሩን/ሯን አደፋፍር::

3-------- ስለ ባቡሩ የተሰጠውን መረጃ አንብብ

4-------- ከዚህ ወዲህ ከሚለው በመጀመር ሦስቱን የክለሳ ዐረፍተ ነገሮች ከልሳቸው(አንብብ)::አምስቱን እውነቶች ከልስ::

ለደቀ መዝሙርህ የየዕለት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍለ ጊዜና ጸሎት ጊዜ መውሰድ እንዲጀምር ሐሳብ ስጠው::የየዕለት መጽሐፍ ቅዱስ ምንባብና የጸሎት ክፍለ ጊዜ ለአንተ ምን ትርጉም እንዳለው አብራራለት::

የጽሞና ማስታወሻዎችን አስተዋውቅ (በፓኬት ውስጥ ከሚገኘው):: 3በ5 የሆነውን ካርድ በመጠቀም በአምስቱ እውነቶች ውስጥ ያሉትን የጽሞና ጊዜ ደረጃዎች እንዴት ሥራ ላይ ማዋል እንደሚቻል ለደቀመዝሙርህ አሳየው::

ደቀ መዝሙርህን

- በዚህ ሳምንት ውስጥ የግል ምስክርነቱን ለአንድ ሰው እንዲያካፍል
- የወንጌል ትራክት ለአንድ ሰው እንዲሰጥ ወይም እንዲያካፍል(ስለ ወንጌል ትራክት ለደቀመዝሙርህ አስተዋውቅ ወይም ስጠው)
- የዚህን ትምህርት እውነት ለአንድ ሰው እንዲያካፍል አደፋፍረው ::

የማጠቃለያውን ጥያቄ በመጠየቅ ክፍለ ጊዜውን ፈጽም ስለሚቀጥለው ትምህርት ፍላጎትን ለማነሳሳት ሆን ተብሎ የታቀደ ነው:: ደቀመዝሙርህ አዲስ አማኝ ከሆነ

- ወደ በተክርስቲያንህ ጋብዘው /ጋብዣት (አብራችህ ለመሄድ ጠይቀው/ጠይቃት )

አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዳለው/ላት አረጋግጥ

( ካልሆነ አንተ ካለህ ውስጥ አንዳቸውን ለማዋስ ወይም አንድ ለመግዛት ፈቃደኝነትህን ግለጽ)



# እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ

## ትምህርት 2. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ስለማድረግ

ህብረታችን ከአባት ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው::
1ዮሐ 1:3

**አስታውስ:-** ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት አስተማማኝ ነው:: ምክንያቱም በክርስቶስ ይቅር ተብለሃል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አግኝተሃል::

ይህንን አስተማማኝ ግንኙነት ከመሥጠት በተጨማሪ እግዚአብሔር ከርሱ ጋር በቅርበት እንድትራመድና ቀኑን ሁሉ ከእርሱ ጋር ሕብረት እንድታደርግ ደግሞ ይፈልጋል::

ኃጢአት ስማድረግ ስንመርጥ ግንኙነታችን (እንደ እግዚአብሔር ልጅ ያለን ስፍራ) አይነካም (1ኛ ጴጥ. 1:3-4/ ዮሐ. 10:27-29) ነገር ግን ህብረታችን ይቋረጣል::

ምሳሌ አድርገን የምንወስደው የአባትና የልጅ ግንኙነት ነው::

ከምድራዊ አባት ጋር ያለህ ግንኙነት ቋሚ ነው:: ምንም አድርግ ምን ምንጊዜም የምድራዊ አባትህ ልጅ ነህ:: ነገር ግን ለምሳሌ በአባትህ ላይ በማመጽ በቁጣ ቤቱን ጥለህ ሄድክ እንበል::

እስከ አሁንም ድረስ ያባትህ ልጅ መሆን ትችላለህ ወይ?

በግንኙነትህ ላይ ምን ተፈጠረ? (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ)

### ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነትን ከርሱ ጋር ካለህ ኅብረት

| ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት | ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ሕብረት |
|---|---|
| 1. ክርስቶስን ስትቀበል ጀምሮአል ዮሐ. 1:12 | 1. ክርስቶስን በምትቀበልበት ጊዜ ጀምሮአል ቆላ.2:6 |
| 2. ዘላለማዊ ነው 1ጴጥ.1:3-4 | 2. ሊታቀብ ይችላል መዝ.32:3-5 |
| 3. በእግዚአብሔር የተጠበቀ ነው ዮሐ. 10:27-29 | 3. በከፊል በአንተ ተጠብቋል 1 ዮሐ 1:9 |
| 4. ከቶ አይለወጥም ዕብ. 13:5 | 4. ኃጢአት ስትሠራ ይለወጣል መዝ.66:18 |

ምንም እንኳ ሁሉም ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ቢኖራቸውም ነገር ግን ሁሉም ክርስቲያን ከእርሱ ጋር የማያቋርጥ ሕብረት እየተለማመዱ አይደሉም:: ይህን ሕብረት ባለማቋረጥ መጠበቅ የምንችለው እንዴት አድርገን ነው?

## 1. ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን ሕብረት ሊያግድ የሚችለው ምንድነው?

ለክርስቲያኖችም ሆነ ክርስቲያን ላልሆኑት ኃጢአት ማገጃ ምክንያት ነው::ኃጢአት ሁላችንም የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዳንለማመድ ያግደናል::ነገር ግን ብዙ ሰዎች ኃጢአት በሆነውና ኃጢአት ባልሆነው ነገር መካከል የተምታታ ነገር አላቸው::

**ኃጢአት ምንድነው?**

☞ ኃጢአት ከማታለል፣ከመዋሸት፣ርኩስ ከሆነ ባሕርይ ወዘተ በላይ ነው::እነዚህ ምግባሮች የኃጢአት ዝንባሌ ውጤት ብቻ ናቸው:: ኃጢአት እግዚአብሔር ከሚፈልገው ሕይወትና አካሄድ ይልቅ እኔ የምፈልገውን ማድረግ ነው::ከእግዚአብሔር መንገድ ይልቅ በእኔ መንገድ፣በእኔ ሃሳብ፣በእኔ ዝንባሌና ተግባር የሚመራ ነው::ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጥገኝነት ተላቅቆ መኖር ነው::ይህም ግልጽ በሆነ ዐመፃ ወይም የምንቸገረኝነት መንፈስ የሚገለጽ ነው::

**የኃጢአት ውጤቶች ምንድን ናቸው?**

☞ ክርስቲያን ላልሆኑት ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግን ያስቀራል:: ኤፌ.2÷1-3



ጥሩ ሥነ-ምግባር ያለውን ኑሮ በመኖር ወደ እግዚአብሔር መድረስ የሚፈልጉ ሰዎች እስካሁን ከእግዚብሔር ተለይተ ዋልን?

ለምን ተለይቷል ወይም ለምንስ አልተለዩም? (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩበት)

☞ ለክርስትያኖች ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ያስቀራል:: 1 ዮሐ.1÷6-8

ማጠቃለያ:- ሁለችንም ኃጢአት እንሠራለን:: ስለዚህ እያንዳንዳችን ለኃጢአተኛ አስተሳሰባችን ዝንባሌያችንና ምግባራችን የእግዚአብሔርን ይቅርታ ማግኘት ይኖርብናል::

## 2. ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ለማድረግ መሠረቱ ምንድን ነው?

1ኛጴጥ. 3÷18 አንብብ

የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢውን ሕብረት ለመፍጠር የሚያስችለን የኃጢአት ይቅርታ መሠረት ነው::እንደዚሁም ከእግዚአብሔር ጋር በየዕለቱ ሕብረትን ለማድረግ ለሚያስችለን የኃጢአት ይቅርታ መሠረት ነው::

> «እናንተም በበደላችሁና ስጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል::»
>
> ቆላ 2:13-14 (ከሕያው ቃል)

ይህ በተጻፈበት ጊዜ የኃጢአት መዘርዝሮች ማለት በወይኒ ቤት መዝጊያ ላይ የተሰቀሉ ስያሜ የተሰጣቸው ጥቅል ማለት ነው:: እሥረኛው በደለኛ የሆነበትን ማንኛውም ወንጀል ይዘረዝራል:: እሥራቱም ሲስተናገድ ወይም ለቅጣቱ ዕዳ ሲከፈል ባለሥልጣናት ዝርዝሩን አስወግደው በሙሉ ተ ከፍሎአል ብለው ይጽፋሉ:: እሥረኛው ለእነዚያ ወንጀሎች እንደገና እንዳይከሰስ እንደማስረጃ ይጠቀምባቸዋል:: ክርስቶስ ለኃጢአታችን የተጠየቀውን ዋጋ መክፈሉን ለሚቀበል አማኝ ደግሞ ክስ የለበትም:: የርሱ ወይም የርሷ ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል:: እርሱ ወይም እርሷ ከእግዚአብሕር ሙሉ ይቅርታ አላቸው:: እንደ ቆላ.2÷13-14 ሃሳብ

1. እግዚአብሔር ለኃጢአትህ ምን አደረገ?
2. ክርስቶስ የሞተው ከኃጢአቶችህ ለስንቶቹ ነው?
3. ክርስቶስ በመስቀል ላይ ላንተ በሞተ ጊዜ ስንቶች ኃጢአቶች ነበሩ በፊትህ የቀሩት? (ከላይ የተሰጡ ሦስት ጥያቄዎችን ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ)

የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ሙላ::

✞ ———→ 19 ———→ 19 ———→

ክርስቶስ ሞተ   አንተ ተወለድህ   ክርስቶስን ተቀበልህ

ሙሉ በሙሉ ይቅር እንደተባልህ ማወቅ በዕለታዊ ኑሮህ ላይ ምን ልዩነት ያመጣል? (ተወያዩበት)



### 3. <u>ከእግዚአብሔር ጋር ያለማቋረጥ ሕብረት በማድረግ መቀጠል የሚቻለው እንዴት ነው?</u>

ምንም እንኳን ለዘላለም ፍጹም ይቅር የተባልክ ብትሆንም እስካሁን ድረስ በኃጢአትህ ላይ መዝመት ያስፈልግሃል:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለማቋረጥ ሕብረት መፍጠር አስፈላጊ ነው::

ራስህን በአባትህ ልጅ ምሳሌ ውስጥ አስገባ በምድራዊ አባትህ ላይ ካመጽህ በቁጣም ቤቱን ለቀህለት ከሄድክ ሕብረታችሁን ለማደስ ምን ማድረግ ይኖርብሃል? በዚህ ምሳሌ መሠረት ከሰማዩ አባትህ ጋር እንዴት አድርገህ ሕብረትህን ማደስ እንዳለብህ እንመልከት 1ዮሐ.1÷9

<u>ኑዛዜ:-</u> ኑዛዜ ማለት ስለ ተፈጸመው ዓይነት ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር መስማማት ማለት ነው:: ይኸውም እግዚአብሐር ስለኃጢአትህ የሚለውን ተመሳሳይ ነገር ማለት መቻል ነው::

እግዚአብሔር ያስብከውን÷የተናገርከውን ወይም የፈጸምከውን ኃጢአት እንደሆነ ወደ አእምሮህ በሚያመጣበት ጊዜ ወዲያውኑ ተናዘዝ::

ኑዛዜ የሚከተሉትን ዓይነት የተወሰኑ ነገሮችን ያካትታል:-

1. የፈጸምከው ኃጢአት እንደሆነ ከእግዚአብሐር ጋር ተ ስማማ (በአንድ ነገር ላይ አትኩር)፣ ኃጢአትህን •ይህና ያ ብለው::
2. እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኩል ቀድሞውኑ ለኃጢአቶችህ በሙሉ ይቅርታ ስላደረገልህ

አመስግነው::

3. ወደ ተሳሳተ ዝነባሌና ድርጊት ሊመራ የሚችለውን የተሳሳተ አስተሳሰብህን ቀይር (ንስሐ ግባ)
4. በሕይወትህ ሊሠራ እንደሚችልና ክርስቶስን ወደ መምሰል እንደሚያመጣህ በማመን ለእግዚአብሐር ተ ገዛ::

እንደ 1ኛ.ዮሐ. 1÷9 5÷14-15 ሃሳብ በእግዚአብሔር ላይ ያመፀ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት መታደሱን በርግጠኝነት ማወቅ የሚቻለው እንዴት አድርጎ ነው?

(ከደቀመዝሙርህ ጋር ተወያዩ)

ኑዛዜ:- ኑዛዜ ማለት የውጤቱ ተካፋይ መሆን ማለት ነው:: የኃጢአት ወቀሳ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው÷ ኩነኔና ሐሰተኛ የበደለኝነት መንፈስ የሚመጣው ከሰይጣን ነው:: ኃጢአትህን ከተናዘዝህ በኋላ እስከ አሁንም ድረስ የበደለኝነት መንፈስ ቢሰማህ ምን ማድረግ ይኖርብሃል? መዝ 32፣1-5 እና ሮሜ 8 ፣1ን አንብብ:: እነዚህ ጥቅሶች ስለ በደለኝነት መንፈስና ስለመንፃት ምን በማድረግ ይናገራሉ? ዕብ 9፣14ን አንብብ:: ይቅርታ ማድረግስ ምን ታደርግ ዘንድ ነፃ የሚያወጣህ ይመስልሃል? (ከደቀመዝሙርህ ጋር ተወያዩ)

ስለ በደለኛነት መንፈስና ስለ ይቅርታ ካየነው እውነት አንፃር የሚከተለውን ዐረፍተ ነገር እንዴት አድርገህ ነው አሟልተህ የምትጽፈው?

ኃጢአቴን በሙሉ በተናዘዝኩበት ጊዜ እኔ ------------------------

------------------------------------------------------------::



4. <u>ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ሕብረት እንዴት ማደግ ትችላለህ?</u>

<u>ዛሬ ማታ ወደ መኝታ ከመሄድህ በፊት:-</u>

1. በሕይወትህ ያለውን ማንኛውም ኃጢአት እንዲገልጥልህ እግዚአብሔርን ጠይቀው::
2. ኃጢአትህን ዝርዝር በቁርጥራጭ ወረቀት ላይ አስፍር:: ይህ በእግዚአብሔርና በአንተ መካከል ያለ ጉዳይ በመሆኑ ፊጸሞ መተማመን ይኑርህ::
3. ቁጣ÷ጥላቻና ምሬት ኃጢአት እንደሆኑ አስታውስ:: ኤፌ 4፣31-32ን አንብብ::

   በሕይወትህ ዘመን በአንድ ወቀት ተጎድተህ ሊሆን ይ ች ላ ል : : ይ ቅ ር ያ ል ተ ባ ለ ጉ ዳ ት ፣ ፣የቁጣ፣የጥላቻና፣የምሬት ባሪያዎች ሊያደርገን ይችላል:: በመጨረሻ ሕብረታችንን ሊበክሉ የሚችሉትን ሌሎች በእኛ ላይ የፈጸሙትን የስህተት ነገሮች ለመያዝ እናዘነብላለን:: ከእንዲህ ዓይነቱ ባርነት ነፃ ልንሆን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይቅርታ ማድረግ ነው:: (በፈቃደኝነት መንፈስ የበደለህን ሰው ከበደለኛነት መንፈስ ነፃ አድርገው) ክርስቶስ የእኛን በደል ይቅር ለማለት ፈቃደኝነቱን ካሳየ እኛስ ማነን? የበደሉንን ይቅር ለማለት እምቢተኛ የምንሆነው? ከጉዳታችንና ከምሬታችን ጋር በመጣበቅ ሊገኝ የምችለው ጥቅም ምንድን ነው? ይቅርታ ለማድረግ ልትታዘዝ ፈቃደኛ ነህ?

4. የበደሉህን ሰዎች ስም ዘርዝር:: ይቅር የምትለው ማንም ቢኖር

ለእያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር ሆይ ምንም እንኳን (የሰውዬውን ስም በመጥራት በፈጸመብኝ በደል ያስከተለብኝ ውጤት ከባድ ቢመስለኝም ይቅር ልለው/ልላት መርጫለሁ::

5. ዝርዝርህን ከጨረስህ በኋላ በላዩ ላይ በ1ኛ ዮሐ.1÷9 ላይ ያለውን የይቅርታ ተስፋ ቃል ጻፍበት::
6. እግዚአብሔርም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባደረገው መስዋዕ ትነት ምክንያት ይቅርታ ስላደረገልህ አመስግነው::

ዝርዝሩን ቀደህ ጣለው::

በዚህ ሳምንት ከእግዚአብሔር ጋር በየቀኑ 15 ደቂቃ ወይም ከዚያ በላይ በመውሰድ ቃሉን በማንበብና በጸሎት ለማሳለፍ ሞክር::

ለዚሁም ከዚህ በታች አንዳንድ አስተያየቶች አሉ::

1. ሉቃ. 15:11-32 ያለውን ክፍል አንብብ:: ታሪኩ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ግኑኝነት ስላገኘነው ይቅርታና ከእርሱ ጋር ላለን ሕብረት ምን ያስተምረናል? (ከደቀመዝሙርህ ጋር ተወያዩበት)
2. ገላ. 5:16-23 ያለውን ክፍል አንብብ:: እግዚአብሔር በሕይወትህ እንዲሠራ ስትፈቅድ ሊታይ የሚችለውን ልዩነት አስተውል::እግዚአብሔርን በማሳዘን ላይ የሚገኘ ውን የሕይወትህ ክፍል ምንነት በተረዳህ መጠን እንደ 1ኛ ዮሐ.1:9 ሃሳብ ወዲያው እርምጃ ውሰድበት ከዚያም ከእግዚአብሔር ጋር ባለማቋረጥ ሕብረት ደስ ተሰኝ::
3. መዝ. 32ን አንብብ::



- በዚህ መዝሙር ስለ ንስሐ የዳዊት ልምምድ ምን ነበር? ኃጢአቱን ከመናዘዙ በፊት እንዴት ተሰማው? በኃጢአቱ ላይ እርምጃ ከወሰደ በኋላስ እንዴት ተ ሰማው? (ተወያዩበት)
- ከበደለኛነት ስሜት፣ከኩነኔ ስሜትና ከተስፋ መቁረጥ ስሜት ጋር ትግል የሚያደርጉ ሌሎች ሰዎች ታውቃለህን? እግዚአብሔርንስ በሕይወት ለማወቅ እንደሚፈልጉ ታውቃለህን? ከጨለማው ዓለም ግዛት ሊያድናቸው ደህንነትንና የኃጢአትን ይቅርታ ወዳገኘ ንበት ወደ ክርስቶስ መንግሥት ሊያመጣቸው ይችላል:: ቆላ.1: 13-14

<u>ማጠቃለያ</u>:- የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታውን መረዳት ክርስቲያኖችን ከርሱ ጋር ባላቸው ባለማቋረጥ በሚያድግ ሕብ ረት ደስ እንዲሰኙ ያደርጋቸዋል::

ታዲያ የተቀደሰ ክርስትና ኑሮ ይኖሩ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠውን ኃይል ብዙ ክርስቲያኖች የማይለማመዱት ለምን ይሆን (በሚቀጥለው ትምህርት ተወያዩበት)

## ትምህርት ሁለትን በሕይወት በመተግበር ሌላውን ሰው ደቀመዝሙር የማድረግ ዝግጅት መመሪያ

- በሕይወትህ የተከሰተውን ማንኛውንም ኃጢአት እንዲገልጥ እግዚአብሔርን ጠይቀው::የኃጢአትህን ዝርዝር ጻፍ፣ቅሬታ ጥላቻና ንዴት ኃጢአት መሆናቸውን አስታውስ::እያንዳንዱን ኃጢአት ተናዘዝ::በአንተ ምትክ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ ኃጢአትህን ሙሉ በሙሉ ይቅር ስላለህ እግዚአብሔርን አመስግነው::ለኃጢአት በሙሉ ክርስቶስ በመስቀሉ ዋጋ መክፈሉን አስታውስ::
- ይቅር እንድትላቸው እግዚአብሔር የገለጠልህን የበደሉህን ያህል ሰዎች በሙሉ ስም ዝርዝር ጻፍ::

| የቅሬታው ምክንያት | ቅሬታው የፈጠረብኝ ስሜት | ስረዥም ጊዜ ያስከተለብኝ ተጽዕኖ ወይም የማካሂደው የመከላከያ ዘዴዬ |
|---|---|---|
| ያለአግባብ መጎዳት | ቁጣ፣ንፁህ ያልሆነ ሀሳና ለአደጋ መጋለጥ፣ክፋት ፊቶት ማጣት፣እፍረት | ሰዎችን አለማመን፣በራስ የዝቅተኛ ነት ግምት፣እግዚአብሔርን የማየት አቅም ማጣት:: |
| ቃልኪዳን ማፍረስ | ቁቃተቢስ መሆን፣ ያለመወደድ፣ መገለል፣ ተ ቀባይነት ማጣት፣ ተፈላጊነት ማጣት:: | ሌሎችን አለማመን፣በሕይወቴ የሚተገበረውን የእግዚአቢሔርን የተስፋ ቃሎችን ለማመን አለመቻ ል |

☞ በተደጋጋሚ የጎዱህን ሰዎች (ከቤተሰብ አባላት:ከጓደኞችህ ከሥራ ጓዴዎች ከመሥሪያ ቤት ባልደረቦች ወዘተ ስም ዝርዝራቸውን ወረቀት ላይ በሦስት ከፋፍለህ ጻፍ:: የበደለኝ ሰው ስሙ (ስሟ) --------------------

☞ ለበደሉህ ሰዎች ይቅርታ የማድረግህን ዝርዝር/ሠንጠረዥ ከዚህ በላይ በተሰጠህ ምሳሌያዊ መመሪያ መሠረት ከጻፍክ በኃላ ለእያንዳንዱ ሰው ለየብቻው ፀልይላቸው:: እያንዳንዱን የበደለህን ሰው ስም እግዚአብሔር ወደ አእምሮህ ላመጣው ለእያንዳንዱ ቅሬታህ ምንም እንኳን የተሰማኝ ለረዥም ጊዜ ተጽእኖ ወይም የመከላከል ዘዴን እንዲቀርጽብኝ ያደረገኝ ቢሆንም ጌታ ሆይ ይቅር ልላቸው መርጫለሁ::በዚያ ግለሰብ ለተፈጠረብህ ለእያንዳንዱ ቅሬታ ደጋግመህ ፀልይ:: ሌሎች ሰዎች ያደ ረሱብንን ጉዳትን ይቅር በምንልበት ጊዜ ስሜታዊ፣ አእምሮአዊና ህሊናዊ ፈውስ ይገኛል:: በግለሰቦች ለተፈጠረብህ በሚታስታውሰው ቅሬታህ ለተጎዳ ስሜትህ



ላሳደረብህ ለረዥም ጊዜ ተጽዕኖ ይቅር ካልክ በኃላ ፀልይ ጌታ ሆይ ከዚህ በኃላ በእነዚህ ላይ ደግሜ ምንም ቅሬታ ላለመያዝ መርጫለሁ:: ከነዚህ ከታሰርኩባቸው (ከንዴት፣ ከመራርነት ወዘተ) ነፃ ስላወጣኸኝ አመስግናለሁ::የተጎዳውን ስሜቴን እንደምትፈውስ ባንተ እታመናለሁ አሁን (የበደለኝን ሰው) እንድትባርከው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶ ስም እጠይቅሃለሁ አሜን!

☞ ይቅር ካልክ በኃላ እግዚአብሔር በዚያ ሰው ላይ ሌላ ይቅር ያላልከው ቅሬታ ወደ አእምሮህ ካመጣ ይቅር ካልክበት የመጨረሻው ቅሬታ ይቅርታ በኃላ የሆነውን ለማስታወስ በየመሥመሩ ዝርዝሩንና ቀኑን መዝግብ:: እነዚህንና ሌ ሎችን እያመጣ ሰይጣን በሚፈታተንበት ጊዜ ሁሉ ያንን ሰው በማሰብ ለወደፊቱ ምንም ቅሬታ በዚህ ሰው ባለመያዝ ይቅር ለማለት ይረዳሃል:: ሌሎች የቅሬታ ትዝታዎች ወይንም ሌሎች አዳዲስ ቅሬታዎች ሲከሰቱ በማስታወሻህ ላይ በመመዝገብ ከላይ በሰፈረው መሠረት ይቅር በለው:: በምትጎዳበት ጊዜ መጎዳት በትኩስ ቁስል ላይ እንደ ተጨመሩ ጨው ስሜት በሚሰማህ ጊዜ እግዚአብሔር በማመስገን የማስታወሻ ዝርዝርህን የምታስወግድበት ወቅት መሆን አለበት::አዳዲስ ቅሬታ ዎችን በዚሁ ሂደት መሠረት ስታስወግድ ለወደፊቱ በንዴትና ይቅር ካለማለት እስራት ቁጥጥር ጨርሶ ነፃ ትሆናለህ:: ማጣት የማትፈልገውን የፅሞና ጊዜ እንዴት ይኖርሃል? ቢያንስ ቀጥሎ ካሉት 3 የምንባብ ክፍሎች አንዱን በሕይወት ተርጉሞ እንዲሁም ከእያንዳንዱ የምንባብ ክፍል ጋር የተያያዘውን ጥያቄ መልስ::

☞ ሉቃ 15: 11-32 (------------------) የጽሞና ጊዜ ጥቅስ
☞ ገላ 5: 16 - 23 (------------------) የጽሞና ጊዜ ጥቅስ
☞ መዝ 32 (------------------------) የጽሞና ጊዜ ጥቅስ

ይቅር ስላልካቸው ሁኔታዎች ምስክርነት ከ2-3 ዓረፍተ ነገሮች በመጻፍ ለክርስቲያን ወይም ክርስቲያን ላልሆኑ ሰ ዎች መስክርላቸው።ይህም አማኝ ጎደኞችህ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘትህን እንዴት እንደአወቅህ ያውቃሉ። ከኩነኔና ከአእምሮ ወቀሳ ሁሉ በአንተ ፋንታ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ምክንያት መሆኑንም ይረዳሉ። ከእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ይቅር መባልህ ሌሎችንም ይቅር ለማለት በቂም፣በጥላቻ ወይም በንዴትና ከስሜታዊ ጉዳት እስራት ነፃ መውጣት እንዳስቻለህ ልትመሰክርላቸው ትችላለህ። ለሁሉም ዘመን ሰዎች ኃጢአት ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት የከፈለውን የኃጢአት ሁሉ ዋጋ የከፈለውንና የፈጸመውን ሥራ ክርስቲያኖችና ክርስትያን ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ ሊረዱ የሚገባ ጉዳይ ነው።ከጥቂት ክርስቲያን ጎደኞች ጋር የይቅርታ ምስክርነትህን ማካፈል አማኞች ላልሆኑ ሰዎች ለመመስከር ድፍረት እንዲኖርህ ይ ረዳሃል።

☞ እንደ አእምሮ ወቀሳ፣ኩነኔ፣ተስፋ መቁረጥ፣ቁጣ፣ጥላቻና ፣ንዴት ያለባቸው ዓይነት ሰዎች በአካባቢህ ሆነው ሲነጋገሩ አድምጣቸው።የይቅርታ ምስክርነትን መስማት የሚገባቸው የእነዚህ ዓይነት ሰዎች መሆናቸውን አትዘንጋ።

☞ ለእነዚህ ዓይነት ሰዎች ምስክርነትህን ለማካፈል አጋጣሚ ዎችን ለማግኘት ፀልይ።

☞ ለምሳሌ:-ይቅር ባለማለት (የአእምሮ ወቀሳ፣ንዴት ወዘተ) ችግር እንደነበረብህ ወይም ከጎዳኞችህ ከአእምሮ ወቀሳ፣ከቁጣ፣ከመራርነት ወዘተ) ነፃ ለመሆን እንደምትችል ይገልጻል። እኔም በነዚህ ነገሮች እችገር ነበር።ከአእምሮ ወቀሳ (ከቁጣ፣ንደት ወዘተ) የእግዚአብሔር ሙሉ ይቅርታ ማግኘቴን ካወቅሁ በኃላ እንዴት ነፃ እንደሆንኩ ላንተ ማካፈል እችላለሁ ወይ? (በማለት ሁል ጊዜ ፈቃድ በመጠየቅ የራስህን የገጠመኝ ታሪክ አካፍል)!!



መልሳቸው አዎን ከሆነ የይቅርታ ምሥክርነትህን ከ2-3 ዓረፍተ ነገር አሳጥረህ ንገራቸው፣እነርሱ ለመስማት ካላቸው ዝግጁነት ይበልጥ በብዛት ከመናገር ይልቅ እነርሱ ለማወቅ ለሚፈልጉት ጉዳይ እንዲጠይቁህ ፍቀድላቸው።

☞ መልሳቸው አሉታዊ ከሆነ እነርሱ በፈለጉህ ጊዜ ተገኝተህ ምስክርነት ልትሰጣቸው እንደምትችል አሳውቃቸው።አሁን እነርሱ አይሆንም በሚሉበት ጊዜ ፈቃደኛ መሆን እነርሱ ለመስማት ፈቃደኛ በሚሆኑበት ጊዜ ቀርቦ ለማካፈል ይ ረዳሃል። እስከዚያ ይቅር መባልና ይቅር የማለት አስፈላጊነት እግዚአቢሔር እንዲያሳያቸው ፀልይላቸው።

☞ ደቀመዝሙርህን ትምህርት 2 በማጠቃለል እርሱ/እርሷ ከላይ ያሰውን የአገልግሎትና በግል ሕይወት የመተግበር ዘዴን እንዲያጠቃልል/እንድታጠቃልል ኃላፊነት ስጠው/ስጣት

☞ አስታውስ ለራስህ ለማከናወን ታማኝነትና ኃላፊነት የማይሰማህን ነገር ለሌሎች እንዲሰማቸው ማድርግ አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ግብዝነት ነው። ስለዚህ የፅሞና ጊዜን፣የደህንነት ምሥክርነትን፣ይቅርታ የማድረግ ምስክነትህንና የወንጌል መመስከሪያ በራሪ ጹሑፎችን ከሌ ሎች ጋር ሆነህ በሥራ ላይ ማዋልህን ቀጥል)!!

<u>ብዙውን ጊዜ ከቁጣ፣ ከፍርሃት፣ ከጭንቀት፣ ከኃጢአት . . . ወዘተ ስሜቶች መፈራረቅ በተጨማሪም)</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ተስፋ መቁረጥ | • መገለል | • መምታታት | • መጠመድ |
| • መደፈር | • መውቀስ | • አለመረዳት | •አስቀያሚነት |
| • ፍራት | • ረዳት አልባነት | • ፍቅር ማጣት | •ተቀባይነት ማጣት |
| • ብቸኛነት | • ተስፋቢስነት | • አቅመቢስነት | • አለማመን |
| • ያለመመቸት | • ዝቅተኛነት | • ተቃውሞ | • መጠቆሚያ መሆን |
| • ክህደት | • ቸልተኛነት/ ስንፍና | • ስህተትን መቀበል | • መጣላት |
| • አቅም ማጣት | • አለመብቃት | • አስፈሪነት | • ሆደባሻነት |
| • እፍረት | • ዋጋቢስነት | • አጋጣሚን መጠቀም | • ተገቢነት ማጣት |

(የመሳሰሉት ለበደሉን ይቅርታ ባናደርግ የሚገጥሙን ናቸው)

# የመሪዎች መመሪያ

## 2. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ

የክፍለ ጊዜው ትኩረት :-

እምነትህን በእርሱ ላይ በሚኖርና በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ፈጽሞ ይቅር ተብለሃል:: ኃጢአትህን በተናዘዝህ ቁጥር ከእግዚአብሔር ጋር ያላሰለሰ ኅብረት አለህ (ፍቅሩንና ይቅርታውን ተለማመድ)

ዝግጅት :-

በትናንሽ ፊደላት የተጻፉትን ጥቅሶች በሙሉ ክልስ:: በኑዛዜ ላይ የተሰጠውን ትምህርትና በግንኙነትና በኅብረት መካከል ያለውን ልዩነት እወቅ::

ግንኙነት መሥርት :-

ባለፈው የግንኙነት ጊዜ ግለሰቡ ስለነገረህ ነገር ( መንፈሳዊ ያልሆነ ) ጠይቀው :: ከግለሰቡ ጋር የተገናኘ ጥያቄ ልታዳምጥና ልታስታውስ እንዳለህ ያሳያል::

ወደ ርእሱ ሽግግር :-

« ካለፈው ሳምንት ትምህርት የመጽፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዳቸውን ለማየት ዕድል ነበረህ?» በማለት ጠይቅ:: ስለባለፈው ሳምንት ውይይት ጥያቄዎችን ለመጠይቅ ለግለሰቡ ዕድል ስጠው:: የጽሞና ጊዜ ደረጃዎችን ሞክረሃል?ብለህ ጠይቀው :: በቃሉ ውስጥ ላሉት ብዙ እውነቶች እግዚአብሔርን እያመሰገንክ በአጭሩ ጸልይ::

ትምህርት ወረቀቶችን መጠቀም :-

በወረቀቱ ላይ ያለውን የመጀመሪያ ገጽ በማንበብ በማህል ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ :: የግንኙነትና ህብረት መግለጫ



ካነበብህ በኃላ አንዳች ጥያቄ ቢኖር አንሣ :: ከሌለም በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች ተመልከት :: ሽግግር ለመፍጠር በገጹ ግርጌ ያለውን ዐረፍተ ነገርና ጥያቄ ተጠቀም ::

1——— ኃጢአት ምን እንደሆነና አማኞችንም ሆነ ያለሙትን እንዴት እንዳሚጎዳ ማየት በሚያስችለው ነጥብ ላይ አተኩር:: እንደ ኤፌ 2:103 አሳብ ሰዎች ጥሩ ?ሥነ ምግባር ያለውን ህይወት በመምራት ወደ እግዚአብሔር መድረስ አይችሉም :: ምክንያቱም በመንፈስ ሙታንና በተፈጥሮ የቁጣ ልጆች ናቸው::

2——— ደቀ መዝሙርህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል መመለስ አለበት ::

- እግዚአብሔር ኃጢአቶችህን ምን አደረገ? (ይቅር ብሎአል)
- ለስንቶች ኃጢአቶችህ ክርስቶስ ሞተ ? ( ለሁሉም ) ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስላንተ በሞት ጊዜ ስንቶች ሀጢአቶች ነበሩ በፊትህ የቀሩት (ምንም አልቀረም) በጊዜው መስመር ላይ ደቀመዝሙርህ ተወለደበትን ጊዜና ክርስቶስን የተቀበለበትን ጊዜ ሞልቷል (ለምሳሌ 1950-1985):: ከመለወጣችን በፊት ለሰራናቸው ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ ለሁሉም ኃጢአታችን የሞተ መሆኑን አመልክት:: ክርስቶስ በሞተ ጊዜ ሁሉም ኃጢአታችን የወደፊት ነበሩ:: ስለሆነም ሁሉም በእኩል ደረጃ ይቅር ተብለዋል ወይም ተ ደምስሰዋል
    - በየዕለት ኑሮህ አንተ ፈጽሞ ይቅር መባልህን ማወቁ ምን ልዩነት ያመጣል ? (የተለያዩ መልስ ሊሰጥ ይችላል)

3---------ግለሰቡ የሚከተሉትን ሦስት ጥያቄዎች በእግባቡ መመለስ ይኖርበታል::

- ከእግዚአብሔር ጋር ላለው ኅብረትህ መታደሱን እንዴት ማወቅ ትችላለህ? (የእርሱ ፈቃድ ኃጢአታችንን መናዘዝ ነው:: ሊሰማንና ይቅር ሊለን ቃል ገብቷል::)
- እነዚህ ጥቅሶች ስለበደልና ከእነዚህም ስለመንጻት ምን ይናገራሉ ? (ይቅር ተብለሃል፣ እንዳችም ኩነኔ የለም ስለመንጻትህ ከእግዚአብሔር የሚልህን ቃል ስማ በስሜቶችህም አትደገፍ::)
- ይቅርታ ነጻ የሚያወጣህ ምን እንድታደርግ ነው? (እግዚአብሔርን እንድታገለግል)

ኃጢአትን በሙሉ በተናዘዝህ ጊዜ እኔ ----------- የሚለውን ዐረፍተ ነገር መልስ እንዲሞላ ለደቀመዝሙርህ ጊዜ መስጠቱን አትዘንጋ::

4. ------ ይህ ሁል ጊዜ የሚደረግ ሳይሆን ነገር ግን እንዴት ፈጽሞ ቅር እንደተባልን ትኩረታችን ለመሳብ የተደረገ መሆኑን በማመልከት በኃጢአት / መንጻት ዝርዝር ላይ ትኩረት አድርገ:: በሚቅጥለው ጊዜ ስትገናኙ እንደምትነጋገሩበት ቃል ግባ::

በየዕለቱ የጽሞና ጊዜ ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብና ጸሎት ሦስቱ የአምልኮ የምንባብ ክፍሎች መነበብ እንዳለባቸው ሀሳብ ስጥ :: አዲሱን ክርስቲያን እነዚህን ክፍሎች በማውጣት እርዳው::

የመጨረሻው ጥያቄ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ስመለስ ታሳስባለህ:: የሚቅጥለውን የቀጠሮ ጊዜና ቦታ በመያዝ መለያየታችሁን አረጋግጥ::



# እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ

## ትምህርት 3. ለእግዚአብሔር የመኖር ኃይል

> መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና:: ኤፌ. 5:18

እስታውስ:-

> የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ ለመለማመድ ኃጢአትህን ባወቅኸው ጊዜ ወዲያው መናዘዝና ወደ ሰማያዊው አባትህም እንደገና መመለስ እንደሚኖርብህ በትምህርት ሁለት ተከታትለሃል::

በሕይወትህ አስደናቂው ለውጥ መከናወን የጀመረው ክርስቶስን እንደ አዳኝህና ጌታህ አድርገህ በተቀበልክበት ጊዜ ነው:: ከዚያም የምግባር መስኪያ ወይም የግብረገብነት ምልክት እንዲሆን ሳይሆን ከአፍቃሪው ሰማያዊ አባትህ ጋር አግባብ የሆነ ሕብረት ያለውን የክርስትና ኑሮ መኖር ጀምረሃል:: ዮሐ 7: 37-39እንብብ

በተለያዩ ምክንያቶች እግዚአብሔር እንዳቀደው ይህን ኑሮ ለመኖር ለዚህ የሚያበቃውን ኃይል እየተለማመደ ያለው ሁሉም አማኝ አይደለም:: ልክ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በአጠቃላይ የተመሠረተው እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ባደረገው ሥራ ላይ እንደሆነ ሁሉ፣ ድንቅ የሆነውን የክርስትና ኑሮ የመኖሩም ኃይል የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው::

ይህ ኮምፒውተር የተሠራበትን ዓላማ ሁሉ ለመፈጸም የሚያስችለው ኃይል አለው



ነገር ግን የራሱ የሆነ ኃይል የለውም::

በተመሳሳይ ሁኔታ ከክርስቶስ ጋር ባለህ ሕብረት በክርስቶስ ማዕከላዊነት የአዲስ ፍጥረት ኑሮን ለመምራት የሚያስፈልግህ ኃይል ሁሉ አለህ:: ነገር ግን አግባብ ካለው የኃይል ምንጭ የሚያስፈልግህን ኃይል ለማግኘት ያለማቋረጥ መፍቀድ ይኖርብሃል::

1. <u>የኃይልህ ምንጭ - (መንፈስ ቅዱስ)</u>

*መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?*

☞ እርሱ እግዚአብሔር ነው:: 1ቆሮ.2:11-12
☞ ለምን መጣ? በውስጥህ ለመኖር መጣ ሮሜ 8:9
☞ ዓለምን ስለ ኃጢአትና ስለ ፍርድ ለመውቀስ መጣ ዮሐ.16:8
☞ ወደ እውነት ሁሉ ለመምራት ዮሐ.16:13
☞ ክርስቶስን ለማክበር ዮሐ. 16:14

ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት መንፈስ ቅዱስ የሚጫወተው ሚና ምን ዓይነት ነው?

ሮሜ 8:14-16 ያለውን ክፍል አንብብ::

1. በሕይወትህ ሊያፈራ የምትፈልገው ምን ዓይነት ፍሬ ነው? ገላ. 5:22-23ን አንብብ::
2. እነዚህን ባሕርያት በሕይወትህ ትፈልጋለህ?
3. በሕይወትህ ፍሬ ለማየት ምን ማድረግ አለብህ? ዮሐ.15:4-5 አንብብ
4. መንፈስ ቅዱስ ምን ለማከናወን ነው ሊያስታጥቅህ የሚፈልገው? የሐዋ.1:8 አንብብ::
5. ለአንተ የክርስቶስ ምስክር መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
6. ለምስክርነት አገልግሎት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያስፈልጋል ብለህ ለምን ታስባለህ? ዮሐ.16:8 አንብብ

(ከተራ ቁጥር 1-6 ያለውን ከደቀመዝሙርህ ጋር ተወያዩ)



ማጠቃለያ:- በክርስቲያች ሕይወት እነዚህ የቅድስና ባሕርያት የተገለጠበት ደረጃ በእያንዳንዱ ዝርዝር የሕይወታቸው ጉዳይ በጌታ ላይ የቱን ያህል እንደታመኑና ለምንስ ያህል ጊዜ በዚህ ሁኔታ እንደሚቆዩ በሚያስገነዝበው እውነት ላይ ይመሰረታል::

የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት መረዳት የጀመረ አንድ ሰው ለረጅም ጊዜ ይህን እውነት እንደተለማመዱት የበሰሉ ክርስቲያኖች ባይሆን ተስፋ ሊቆርጥ አይገባም::

እግዚአብሔርን ማመን + ጊዜ = መንፈሳዊ ብስለት

2. <u>ያንተ ምርጫህ ምንድነው? የእርሱ ኃይል ወይስ ያንተ?</u>

ክርስቲያን የሆንከው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማካኝነት ነው:: ኤፌ.1:13 ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ይኖራል:: ዮሐ.14:16-17:: እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒቱ አድርጎ በተቀበለ በእያንዳንዱ ሰው ይኖራል:: ምንም እንኳን እውነተኛ ክርስቲያን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ የሚኖርበት ቢሆንም ሁሉም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ ሕይወት የሚለማመድ አይደለም:: ስለ ሁሉት ዓይነት ሰዎች የተባለውን ከ1ቆሮ.2:14-16 አንብብ::

| ሀ. ተፈጥሮአዊ ሰው | ለ. መንፈሳዊ ሰው |
|---|---|
| ክርስቲያን ያልሆን (ያለ ክርስቶስ ያለ ሰው) የኃጢአቱ ዕዳ እንዲከፈልለት በክርስቶስ ሞት ያላመነ ሰው ሲሆን መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ውስጥ አያድርም:: | ክርስቲያን (በክርስቶስ ያለ ሰው) ክርስቶስን እንደ አዳኙ አድርጎ የተቀበለና የክርስትና ሕይወቱን ለመምራት በመንፈስ ለመመራት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚታመን ማለት ነው:: |
| በራስ ማዕከላዊነት የሚመራ | በክርስቶስ ማዕከላዊነት የሚመራ |



እ - በእኔነት ቁጥጥር ያለ ሕይወት

✞ ክርስቶስን ባላመነው ሰው ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አይኖርም



✞ - ለክርስቶስ የመቆጣጠር ሥፍራ ተሰጥቶታል

እ - እኔነት ለክርስቶስ አመራር ተገዝቷል

በእኔነት ላይ የተማከለ ህይወት



✞ - ክርስቶስ በአማኙ ሕይወት ይኖራል

እ - እኔነት ራሱን በክርስቶስ አመራር አላስረከበም እኔነት ሕይወቱን ይቆጣጠራል።

1ኛ ቆሮ.3:1-3:1ቆሮ.14:20 አንብብ።ሦስተኛው ክብ ልክ በዓለም ሰው ክርስቲያን የሚያስበውንና የሚፈጽመውን በምሳሌ እያቀረበ ነው። እነዚያ ሰዎች በክርስቶስ ሕፃናት ናቸው። ከክርስቶስ ጋር ሊኖር በሚገባቸው የሕይወት እርምጃ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የማይመሩ ዓይነት ሰዎች ናቸው። የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ ከሆነው ከእርሱ ፍላጎት ይልቅ ለእኔነት ፍላጎት የተረቱ ናቸው።

ከእነዚህ ከ3ቱ ዓይነት ክቦች ያንተን ሕይወት የሚወክለው የትኛው ነው? (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ)

3. <u>በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ልትሞላ ትችላለህ</u>

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በምትሞላበት ጊዜ በአንተ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት የራሱን ሕይወት በሚገልጸው በክርስቶስ ማዕከላዊነት የተመራ ትሆናለህ። በእምነት በአንተ ውስጥ ፍሬያማ ሕይወት ለማፍራት ቃል በገባልህ እግዚአብሔር በማመን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሞላት (መመራትና ኃይል ማግኘት)



ትችላለህ። የሚከተሉትን ነገሮች መፈጸም ብትችል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ ሕይወት ልትኖር ትችላለህ።

☛ <u>በመናዘዝ</u>

የምታወቀውን ኃጢአትህን ሁሉ ተናዘዝ። መዝ. 66:18 ልትናዘዝ የሚገባህን ኃጢአት ሁሉ ወደ አእምሮህ እንዲያመጣ በሚችል በመንፈስ ቅዱስ እመን። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመሞላት ስትፈልግ የምታወቀውን ኃጢአት ሁሉ መናዘዝ የሚያስፈልገው ለምን ይመስልሃል? (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ)

☛ <u>በማስረከብ</u>

እያንዳንዱን የሕይወትህን ክፍል ለክርስቶስ አስረክብ ሮሜ 6÷12-13 ዋነኛው የሕይወትህ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? እያንዳንዱን የሕይወትህን ክፍል ለክርስቶስ ማስረከብ ምንና ምንን የሚያካትት ይመስልሃል?

☛ <u>በማመን</u>

<u>እንዲሞላህ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታመን።</u>

1. እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንድትሞላ ትእዛዝ ሰጥቶሃል። ወደ ጥፋት የሚመራችሁ ስለሆነ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይልቅስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። ኤፌ.5:18
2. እንደ ፈቃዱ የሆነውን ልመናህን ስለመመለስ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶልሃል። 1 ዮሐ. 5:14-15

በእምነት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል መሞላት ትችላለህ::
ይህ ጸሎት እምነትህን ለመግለጽ ጥሩ መንገድ ነው::
ውድ አባት ሆይ፡ የራሴን ሕይወት በመምራት በአንተ ላይ ኃጢአት ፈጽሜአለሁ:: ኃጢአቴን ይቅር ስላልክ አመሰግንሃለሁ:: የሕይወቴን ኃላፊነት ተረከብ:: ልታዘዝህ እፈልጋለሁ:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደምትሞላኝ አሁን አምናለሁ ቃል እንደገባህልኝ በእምነት ብጠይቅ ሕይወቴን ስለምትረከብና በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ስለምትሞላኝ አመሰግናለሁ ፡ አሜን!

ይህ ጸሎት የልብህን ፈቃድ ይገልጻልን?

ይህንን ጸሎት አሁኑኑ ብትጸልይ ምን የሚሆን ይመስልሃል?

ይህ የልብህ ፈቃድ ከሆነ ይህንን ጸሎት መጸለይና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ትችላለህ:: (ለደቀመዝሙር አድራጊህ ግለጽ)

## 4. ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሞላት ትችላለህ

በዚህ ሳምንት በኃጢአት ምክንያት በአመጽ ሥራ ወይም በእኔነት ፈቃድ ሕይወትህን መቆጣጠርህን ካረጋገጥህ በቀላሉ መንፈሳዊ እስትንፋስ ተንፍስ:: (ንጹህ ያልሆነውን አስወጣ ንጽሁን ደግሞ አስገባ):: ይህ አስፈላጊ የሕይወት ልምምድ የክርስቶስን ፈቃድ የሆነ ቁጥጥር በመለማመድ ለመቀጠል ያስችልሃል::

**ማስወጣት**:- ኃጢአትህን ተናዘዝ::(1ዮሐ.1:9:ዕብ.10:1-25)

1. ኃጢአትን እንዳደረግህ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማማ (የተወሰኑ ኃጢአቶች መፈጸምህን አምነህ ተቀበል)
2. እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት ፍጹም ይቅርታ ስለሰጠህ አመስግነው::
3. ወደ ተሳሳተ አመለካከትና ተግባሮች ሊመራህ የሚችለውን አስተሳሰብህን ቀይር (ንስሃ ግባ)



በአእምሮአችን ውስጥ እየተካሄደ ያለው መንፈሳዊ ውጊያና ጦርነት አለ (ኤፌ.6:12ን አንብብ):: የርኩስ መናፍስት ኃይላት ሊረቱህና ሊያጠፉህ ይፈልጋሉ አእምሮህን ሁሉ እየማረክህ ለክርስቶስ እንድትታዘዝ መምረጥ አለብህ:: (2ኛቆሮ.10:3-5):: ሰይጣን አስተሳሰባችንን መቆጣጠር ከቻለ ዝንባሌያችንና አድራጎታችንን ሊቆጣጠር እንደሚችል ያውቃል ራስህን ለእግዚአብሔር አስገዛ :: ዲያቢሎስን ተ ቃወም ወደ እግዚአብሔር ቅረብ:: ያዕ 4:5-10 ያለውን ክፍል አንብብ::

**ማስገባት**:- በሕይወትህ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ሙላት በእምነት ጠይቅ:: (ኤፌ.5:18)

1. የሕይወትህን ግዛት ለእርሱ ለመንፈስ ቅዱስ በመስጠት ራስህን ለእግዚአብሔር አስረክብ:: (መዝ.139: 23-24)
2. በአሁኑ ጊዜ መንፈስ ቅድስ እንደሚመራህ እመን (ሮሜ.6:12-14 ያለውን ክፍል አንብብ)::

**ማጠቃለያ**:- ስምህን ክፍት በሆነው ቦታ ሙላ

«እኔ (____________________) ከክርስቶስጋር ተሰቅያለሁ እንደዚሁም እኔ (____________________) አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ነገር ግን ክርስቶስ በእኔ ይኖራል በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሣልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ በማመን በተገኘው ሕይወት ነው:: (ገላ.2:20)::

**አካሄድህን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ ቀጥል።**

1. ዮሐ.8:31-32ን አንብብ ። ስለ እግዚአብሔርና ስለራስህ ሕይወት ያለውን እውነት ማወቅ ለምን ያስፈልጋል?
   ከአንዳንድ የኃጢአት ልምምዶች በመላቀቅ ነጻ መውጣት የሚፈልጉ ሌሎች ሰዎችን ታውቀለህ? ይህንን እውነት ብታካፍላቸው በደስታ የሚቀበሉ ይመስልሃል?
2. ኤፌ.5:18-21 እና ቆላ 3:12-17 ያለውን ክፍል አንብብ።እነዚህን ሁለት ክፍሎች ስታወዳድር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለተሞላ ሕይወት ምን ይናገራሉ?
3. በኤፌ. 3:18-21 ያለውን የጳውሎስን ጸሎት አንብብ። ለንደኞቹ የተመኘው ኃይል ምንድን ነው? ይህ ኃይል ከየት ይመጣል ለእኛስ ምን ያደርጋል?
4. እንክብካቤውን በተጠራጠሩ ጊዜ በማዕበሉ ውስጥ የነበረውን የደቀመዛሙርቱን ታሪክ አንብብ። ለምን ነበር የፈሩት? እግዚአብሔርን በተመለከተ ጥርጣሬያቸው ምን ነበር?

(ከላይ የተሰጡ ጥያቄዎችን ከደቀመዝሙርህ ጋር ተወያዩ)

> እንድን ሰው ማመን የሚትችለው ባወቅኸው መጠን ብቻ ነው። ስለሆነም በክርስትና ሕይወት ማደግ ትችል ዘንድ እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ እንድታውቀው ያቀደልህ እንዴት እንደሆነ በሚቀጥለው ትምህርት ታገኛለህ።



**ትምህርት ሦስትን በግል ሕይወት በመተግበርና ደቀመዝሙርን የማዘጋጀት መመሪያ**

☞ በየጊዜው ሕይወትህን ለክርስቶስ በማስረከብ ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ቁጥጥር ሥር ኑር።የጥሞና ጊዜ የምንባብ ክፍሎችህን ስታነባቸው በእያንዳንዱ ቀን ማስወጣትና ማስገባትን ለማብራራት የተሰጠውን መግለጫ ክልስ። ለእእምሮህ ውጊያ የሚለው ክፍል የበለጠ ትኩረት በመስጠት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እንደ አስፈላጊነቱ ክልስ። በአሁኑ ወቅት በገላቲያ 2:20 ባለው ክፍል ስምህን ማንበብና ትክክለኛ የሕይወት መግለጫ መሆኑን ማወቅ ትችላለህ? ካልሆነ ኃጢአትህን/የራስህን ፈቃድ ተናዘዝና ለክርስቶስ የፍቅር ቁጥጥር ሕይወትህን አስረክብ።

☞ ማጣት የማትፈልገውን የጥሞና ጊዜ የምታገኝበትን ዘዴ ቢያንስ ቀጥሎ ከሁለት የምንባቡ ክፍል ጥቅሶች አንዱን በሕይወትህ ተለማመድ። እንደሁም ከእያንዳንዱ የምንባቡ ክፍል ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን መልስ።

ዮሐ 8:31፣32 (--------------------------------) የጥሞና ጊዜ ጥቅሶ
ኤፌ 5:18-21 (--------------------------------) የጥሞና ጊዜ ጥቅስ
ቆላ 3:12-17
ኤፌ3:14-21 (--------------------------------) የጥሞና ጊዜ ጥቅስ
ማር4:35-41 (--------------------------------) የጥሞና ጊዜ ጥቅስ

☞ እያንዳንዱን የሕይወትን ክፍል ለይተህ ለክርስቶስ በማስረከብ ክርስቶስ በራሱ ቅደም ተከተል ዘዴ እንዲያስተካክል ለእርሱ ፈቀደለት።

☞ ሦስቱን ክቦች ከነማሸጋገሪያ መስመሮች፣ዓረፍተ ነገሮች በደቀመዝሙር አድራጊው መምሪያ ላይ ከቀሩቡት ጥቅሶች

ጋር ክልስና ለምስክርነት ለመጠቀም ተዘጋጅ::

«ኢየሱስን ተቀበል» ከሚለው መሥመር በታች የዘለልናቸውን ዮሐ 1:12 እና ራዕ 3:20 ጨምረህ ክልስ::

☞«ሦስቱ ክቦች» በመሳል ለበርካታ ክርስቲያን ጎደኞችህ ወይንም ላላመኑት የማሸጋገር መስመሮችን፣ዐረፍተ ነገሮችንና ተገቢ የሆኑ ጥቅሶችን በተገቢ ቦታ በማስገባት በተፈጥሮአዊ፣መንሳዊና ሥጋዊ ሰው መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት አሥረዳቸው:: (ሦስቱንም ክቦች ያለመሻጋገሪያ መሥመሮች ዐረፍተ ነገሮች ወይም ጥቅሶች ሣላቸው) እነዚህ ሦስቱም ክቦች በማንኛውም ጊዜና ወቅት እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው እንዴት እንደሚመለከት የሚያብራሩ ናቸው:: የመጀመሪያው ልዩነት በሕይወታቸው ክርስቶስ በሌላቸው (ወደ ግራ ክብ አመልክት ክርስቲያን ያልሆኑ) ክርስቶስ ባላቸው(በቀኝ በኩል ወደ 2 ክቦች አመልክት ሁለቱም ክርስቲያኖች)መካከል ነው የታየው ልዩነት::ሁለተኛው ልዩነት የተደረገው ክርስቶስ በሕይወታቸው ባላቸው ሁለቱ ክቦች መካከል ነው:: ከላይ በቀኝ በኩል ያለው ክብ (ወደ ክቡ አመልክት) ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ያመኑና ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የፍቅር አመራርና ንብረታቸውን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ያስረከቡትን ለማብራራት የቀረበ ነው:: በስተቀኝ ከታች ያለው ክብ (ወደ ክቡ አመልክት) ሕይወታቸውን ለክርስቶስ በማስረከብ በፍቅሩ፣በጥበቡና በኃይሉ ከመቆጣጠር ይልቅ ሕይወታቸውን በራሳቸው ለመምራት የመረጡትን የሚያብራራ ነው::

በዚህ እውነት ውስጥ የሚያስደንቀው ነገር ራስ ወዳድ የሆኑ ክርስትያኖች ሕይወት በስተ ግራ ከታች ወዳለው ክብ መልክት)



አካሄዳቸውንና ተግባራቸውን ልክ እንደምመራ ሕይወት እንዳላቸው እንዳላመኑ ሰዎች ሕይወት(በስተግራ ካላይ ያለውን ክብ አመልክት) መምሰሉ ነው:: እነዚህ ሁለቱም ክቦች ከእግዚአብሔርና በመለኮታዊ ኃይሉ ተለይተው በራሳቸው ምርጫ የሚኖሩትን የሚወክሉ ናቸው:: እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው አንዱን ሰው እንዲደርስላቸው ያቀደውን ሁሉንም በረከቶችን፣ጥቅሞችንና ኃይሉን እንዲያገኝ ያለው በክርስቶስ የተመራ ሕይወት (በስተቀኝ ከላይ ያለው ክብ) ብቻ ነው:: ከዚያም በአሁኑ ሰዓት ከእነዚህ ሦስት ክቦች የቱ ነው ያንተን ሕይወት የሚወክለው? ብለህ ጠይቀው:: አስቦ መልስ እንዲሰጥህ ጊዜ ስጠው:: ከዚያም የትኛው ክብ ሕይወትህን እንዲወክል ትወዳለህ? ብለህ ጠይቀው::

☞ አሁን በሦስቱም ክቦች መካከል ያለውን ግንኙነት የመሸጋገሪያ መሥመር ዓረፍተ ነገሮችን ጥቅሶችን በመጠቀም አብራራቸው:: ከክርስቶስ ውጭ የነበረ ሰው ኃጢአቱን/ቷን በማወቅ፣የክርስቶስን ይቅርታ ተቀብሎ ፣ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኙ/ዋና ጌታ እንዲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወታቸው በመጋበዝ በክርስቶስ የተመራ ሕይወት ሊኖረው ይችላል:: (ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀበል በሚለው አመልካች ሥር ዮሐ 1:12ና ራዕ 3:20ን መጨመር አስታውስ ) አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነ በኃላ ሕይወቱን/ዋን ማን መምራትና ማነቃቃት እንዳለበት ወዲያውኑ መመረጥ ያለበት ጉዳይ ነው:: ያ ሰው በየጊዜው እግዚአብሔርን አለመታዘዝ (ኃጢአት) ማድረግን ወይም ለራሱ/ሷ ባለው/ባላት (የራስ ፈቃድ)

ላይ መደገፍ ፣ሁሉንም የክርስቶስን ጥበብ፣ባሕርያትና ኃይል ይመርጥ ይሆናል:: (1የሐ. 1:8)

- ያ ሰው ኃጢአቱን/ቷን ወይም የራስ ፈቃድ፣ በተገነዘበ ጊዜ ወዲያውኑ ኃጢአቱን ወይም የራሱን ፈቃድ ሳይቶ በመናዘዝ፣ሕይወቱን ለክርስቶስ ቁጥጥር አስረክቦ እርሱን/ሷን በራሱ ባሕሪያትና መለኮታዊ ማንነት እንዲመራና እንዲያነቃቃው እርሱን ማመን ያስፈልጋዋል(1ዮሐ.1:9)::
- እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰጠውን ገደብ የሌለውን ሕይወት ሰው ሁሉ እንዲለማመደው ፍላጎቱ ነው::ቢሆንም ለእያንዳንዱ ሰው የመምረጥ ነፃነት ሰጥቶታል:: የክርስቶስን ይቅርታ ነፃ ሥጦታ ለመቀበል ወይም ለመንፈሱ ፍቅር አመራርና ኃይል ሕይወትህን ለማስረከብ ትመርጣለህ?
- መልስህ አዎን ከሆነ በቃል ቢናገር ለደህንነት በፀሎት ለመምራት ራስህን አስረክብና በክርስቶስ ፍቅር ቁጥጥር ሥር ለመሆን ውዴ የሆንህ ጌታ ኢየሱስ ሆይ እኔ እፈልግሃለሁ:: በራሴ ፈቃድ በመመራት ባንተ ላይ ኃጢአት መሥራቴን አውቃለሁ:: በመስቀል ላይ በመሞት ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ስላልከኝ አመሠግንሃለሁ:: አሁን በእምነት እኔ ስጠይቅህ ባለህበት በዙፋንህ ሆነህ ሕይወቴን ተቀበል:: አሁን ሕይወቴን ለመምራትና በመንፈስ ቅዱስ ስለአነቃቃኸኝ አመሰግንሃለሁ::
- አስደናቂውን በመንፈስ የተሞላ ሕይወት ተለማምዳሃል? የምለውን ለማያዊውን መጽሔቴን ለበርካታ ክርስቲያን ጎደኞችህ ማካፈል ከተለማመድህ ክርስቲያን ላልሆኑ ወይንም ለማንኛውም ክርስቲያን ነኝ ለሚሉት/ትል



ሃይማኖተኛ መመስከር ድፈረት ታገኛለህ:: የምትመሰክርላቸው ሕይወታቸውን ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለማስረከብ እንዲችሉ አበረታታቸው::

- እግዚአብሔርን በግል ለማወቅ ትፈልጋለህ? ከሚለው በራሪ ጽሁፍ ይልቅ ሁል ጊዜ በባሕላዊ ክርስቲያን፣ለዘፈቀደ ቤተ ክርስቲያን፣የሚመላለሱ፣ካቶሊክ ሞርሞች፣የሕይሆዋ፣ ምስክሮች፣ወዘተ ይህንን መጽሐፍ መጠቀም ነው::ሰውዬው ከዚህ በፊት የክርስቶስን አዳኝነት ያላመነ ከሆነ ሕይወቱን ለክርስቶስ የፍቅር ጥበቃ አሁኑኑ እንድያስ ረክብ የተፀለየውን የደህንነት ፀሎት ይፀልይ!
- 3ቱን ክቦችና ወይም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት የተሰኘ በራሪ ጽሁፍ ለሌሎች ለማካፈል ብዙ አጋጣሚዎችን ለማግኘት ፀልዩ:: በየጊዜው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመመላለስ አስፈላጊነት ነው:: እስክያውቁ ድረስ ክርስቲያኖች አቅመቢስ፣የተሸነፉና ለምስክርነት የማይበቁ ይሆናሉ::

ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ እጅግ ተፈላጊ ነገር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መመላለስ ጉዳይ ነው::

- ከላይ በትምህርት ሦስት የቀረቡትን በሕይወት የመተግበር እና የአገልግሎት ዘዴ በሙሉ በማጠናቀቅ ለደቀመዝሙርህ ኃላፊነት ስጠው/ስጣት::

አስታውስ:- ለራስህ የማታደርገውን ሌሎች እንዲያደርጉ ማስገደድ አስቸጋር ነገር ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ግብዝነት ነው:: ስለዚህ የጥሞና ጊዜህን ለሌሎች መመስከርን፣3ቱን ክቦችን፣እና የወንጌል ምሥክርነትና የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት በራሪ ጽሁፎች ለሌሎች ማካፈልን ቀጥል::

# የመሪዎች መመሪያ

## 3. ለእግዚአብሔር ለመኖር የኃይል አስፈልጊነት:-

የክፍል ጊዜው ትኩረት :-

የክርስትናን ሕይወት ለመኖር መንፈስ ቅዱስ የኃይል ምንጭ ነው:: እንደዚሁም እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈሳዊ እስትንፋስን በሚለማመድበት ጊዜ ኃይሉን በእምነት የራሱ ማድረግ ይችላል::

ዝግጅት:-

በትናንሽ ፊደል የተጻፉትን ጥቅሶች አንብብ :: ከሦስቱ ክቦች ጋር ተዋወቅ :: በግል ባለህ መንፈሳዊ እርምጃ ላይ አሰላስል::

ግንኙነት መሥርት:-

ባለፈው ሳምንት ክንውኖች ላይ በአንድነት ተነጋገሩ::

ኃጢአት / መንጻት የሚለውን ዝርዝር ጠቃሚ ሆኖ አግኝተኸዋልን?

ወደ ርዕሱ ሽግግር :-

ኃጢአትህን በመናዘዝ ወደ ኃጢአት የሚመራውን የተሳሳተ አሳብን መቀየር ስለመምረጥ የራስህን ልምድ አካፍል::

የትምህርትን ወረቀት መጠቀም:-

በወረቀቱ ፊት ለፊት ገጽ ላይ የሚገኘውን ክፍል አንብብ:: ግለሰቡ ዮሐ.7:37-39 እዲያወጣና እንዲያነብ አድርግ ::

1.------- በትንንሽ ፊደል ጥቅሶ የተጻፉትን ጥቅሶች ብቻ በማንበብ ጥያቄዎቹን መልስ:: እነዚህ ነጥቦች በተ መስከተ የተወሰኑ ጥያቄዎች ሲኖሩ ብቻ በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች ማየት ይቻላል:: ሰዎች ራሳቸውን ለማሻሻል ከሚጠቀሙት ልማዳዊ ዘዴ



እንጻር እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ፍሬ ለማፍራት የሚጠቀምበትን ሂደት ለማነጻጸር ትፈልግ ይሆናል::

- ሮሜ 8:14 - 16 ( እኔ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንኩ መንፈስ ቅዱስ ያረጋግጣል)
- ሮሜ 15:4-5 (በክርስቶስ ኑሩ ፣እደሚገባ ተጣመሩ፣እረፉ ፣ተደገፉ፣በክርስቶስ ጽኑ)
- የሐዋ. 1:8 ( ምስክር ያየውንና የሰማውን ይናገራል:: ስለ ክርስቶስ እውነት እንደሆነ የምታውቀውን ለሌሎች ተናገር)
- ዮሐ. 16:8 (መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ስለኃጢአት መውቀስ የሚችለው )

2.------- 1ኛ ቆሮ. 2:14-3:3 አንብብ :: መስቀሉንና እኔነት ምልክቱን በትክክለኛ ቦታ ለማስቀመጥ እየተጠነቀቅህ ገለጻ በምታደርግበት ጊዜ በእያንዳንዱ ክብ ስዕል ውስጥ ሙላ::




ግለሰቡ ከተፈጥሮአዊ ወይም ከመንፈሳዊ ክብ አንዳቸውን ቢመርጥ ምክንያቱን ጠይቅ:: አላማው ግለሰቡ የት እንዳለ ለይቶ ለማወቅ እንዲችል ለመርዳት ስለሆነ ምርጫውን እንዲቀይር ለማስገደድ መሞከሩን

አስወግድ ። አግባብ ሆኖ ሲገኝ ከክርስቶስ ጋር መራመድ ለአንተ እንዴት ትርጉም ያለው እንደሆነ ልምድህን ለማካፈል ሞክር።

3.------- ግለሰቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል መመለስ ይኖርበታል።

ተናዘዝ :-

በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት የሚታወቀውን ኃጢአት ሁሉ መናዘዝ ለምን ጠቃሚ ነው ብለህ ታስባለህ? (እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ በኑዛዜ አማካኝነት ሆን ብለን ልባችንን እስክምናነጻ ድረስ ከእኛ ጋር ህብረት አያደርግም።)

ራስህን አስረክብ:-

እያንዳንዱ የሕይወትህን ክፍል ለክርስቶስ ማስረከብ የሚያካትተው ምን እንደሆነ አስበሃል ? (በዚህ ነጥብ ላይ ለማሰብ ጊዜ ስጥ ።) በግንዛቤ ላይ፣ በግንኙነት ላይ ፣በሥራዬ ላይ ፣ በልጆቼ ላይ ፣ በመዝናኛ ጊዜዬ ላይ ወዘተ... ክርስቶስ ቁጥጥር እንዲኖረው መፍቀድ የሚከተሉትን መልሶች ጠብቅ ።

እመን:-

- ነጥብ አንድን ካነበብህ በኃላ « በመንፈስ ቅዱስ ትሞላ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ወይ? ብለህ ጠይቅ (አዎን ትእዛዙ ፍቃዱን ያመለክታል ።)»
- ነጥብ ሁለትን ካነበብክ በኃላ «በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ብትጸለይ እንደምትሞላ ታውቃለህን?» ( አዎ እንደፍቃዱ በጸሎት ላይ በመመስረት 1ዮሐ. 5:14-15 )



ይህ ጸሎት አንድ ሰው በመንፈስ የሚሞላ የጥንቆላ አሰራር አይደለም። (በእግዚአብሔር በማመንና በቃሉ አንድ ሰው የመንፈሱን ኃይል የራሱ ማድረግ በመቻሉ ላይ ትኩረት አድርግ )

ይህ ጸሎት የልብህን ፍላጎት ይገልጻልን ?( አሁን ለመጸለይ ወይም ይህን ለማድረግ አመቺውን ጊዜ ለማሰብ ተቀባዩን ግልሰብ ጋብዘው።አትገፋፋው/ት ነገር ግን በሚቀጥለው ጊዜ ስትገናኙ ስለዚህ ነገር ጠይቀው ።

4 ------ በኑዛዜ ዙሪያ ያሉትን ሦስት ጠባያት ከልስ «ማስወጣት» እንደዚሁም «ማስገባት» ማለት ምንድነው በሚለው ሁለት አስተሳሰብ ላይ አትኩር።

ወደሦስቱ ክቦች እንደገና ተመለስ። ከዚህ በታች እንዳለው የሽግግር ቀስትና ዐረፍተ ነገሮችን በማስቀመጥ በተፈጥሮአዊ በመንፈሳዊና በራስ ላይ ባተኮረው ምሳሌ ዎች ማሃል ያለውን ግንኙነት አጠቃልል።

ከጌታ ጋር ጊዜ ወስደህ አሳልፍ የሚለውን አስተያየት ከልስ።

ከዚያም የሽግግሩን ጥያቄ አንብብ ። ለሚቀጥለው የግንኙነት ጊዜ በታውንና ጊዜውን መወሰናችሁን አረጋግጥ።

## እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ

> «እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ» ዮሐ.15:5

### ትምህርት 4. እንደ እግዚአብሔር ልጅ ማደግ

ማስታወስ:

> በክርስቶስ የተመራ ሕይወት እንድትኖር መንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊሰጥህ ይፈልጋል:: በመንፈስ መተንፈስ ስትቀጥል (ማስወጣት ኃጢአትን መናዘዝ : ማስገባት-የመንፈስን ሙላት መጠየቅ) ብስለት ባለው ክርስቲያናዊ ሕይወት እንድታድግ እያስቻለህ ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቀት ያለው ኅብረት ትለማመዳለህ::




### እንደ እግዚአብሕር ልጅ ማደግ ማለት ምን ማለት ነው?

እንደ እግዚአብሔር ልጅ ማደግ ማለት እግዚአብሔርን በሕይወት በማወቅ÷ለእርሱ ባለህ ፍቅር እንደዚሁም ለእርሱ የመታዘዝ ሕይወት መጨመር ማለት ነው:: ዮሐ.17:3ን አንብብ::ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ባሕሪ ምን ዓይነት እንደሆነ ነው የተናገረው? ማቴ22:36-40 አንብብ:: በብሉይ ኪዳን ከ600 በላይ የሚሆኑ ትዕዛዛት አሉ:: ነገር ግን ኢየሱስ በእነዚህ ሁለት ትዕዛዛት አስፈላጊነት



ላይ ያተኮረው ለምን ይመስልሃል?(ከደቀመዝሙር አድራጊህጋር ተወያዩበት)

እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ: ነፍስና (አእምሮ) ሃሳብ መውደድ ከሌሎችጋር ካለህ ግንኙነት እንዴት ያለ ሰውጥ ያመጣል? ዮሐ.14:21 (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ)

ለእግዚአብሔር ያለህ ታዳጊ ፍቅር ውጤት ምን ይሆናል?

### 2. እንደ እግዚአበሔር ልጅ ማደግ የምትችልባቸው መንገዶች?

- ደስ የተሰኘህበትን ሰው ብታገኝ ያንን ሰው በተሻለ ሁኔታ ለማወቅ ምን ታደርግ ይሆን?ከክርስቶስ ጋር ባለህ በየትኛውም ዓይነት ሕብረት መግባባት በጣም አስፈላጊ ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተመራህ በክርስትና ሕይወት ታድግ ዘንድ የሚረዱ አራት የሕብረት መንገዶች አሉ:: እነሱም:-



## መጽሐፍ ቅዱስ

እግዚአብሔር ባህሪውን፣ፈቃዱንና ላንተ ያለውን ፍቅር ታማኝነቱን የሚገልጥበት መንገድ ቃሉ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ነው:: 2ኛ ጢሞ.3:16-17ን አንብብ በዚህ ንባብ ክፍል ውስጥ የተገለጸውን እያንዳንዱን ጠቃሚ ነገር ዘርዝረህ አብራራ::

በንባቡ ክፍል ከሚገኙ ጥቅሞች በዚህ ጊዜ ላንተ በጣም የሚረዱህ የትኞቹ ናቸው? እስካሁን ያከናወንከውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ጥቅም እንዴት አድርገህ ትገመግመዋለህ?

(ለደቀመዝሙር አድራጊህ አብራራው)::

**ጸሎት**:- እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ማድረግን (ምስጋና አምልኮ፣ንዛዜ፣ ልመና በሚመለከት ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት አማካኝነት ትገናኛለህ:: እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ማድረግና ማድነቅ የፍቅር ግንኙነት መግለጫ ነው:: በእውነተኛ መንፈስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንድንችል ዘንድ ክርስቶስ ለኛ አስፈላጊ የሆነውን ዋጋ ከፈለ (ዕብ .10:22) ስለ እርሱ ማንነትና እርሱ ላደረገልን ምስጋናና አምልኮ ለእግዚአብሔር ማቅረብ የሚያስፈልገን ለምንድን ነው?

መዝ 95:6 እና መዝ.150 አንብብ:: ኃጢአትን መናዘዝ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? መዝ.66:18እና 1ኛ ዮሐ.1:9ን አንብብ::(ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩ) አክብሮት በተሞላው ልብ እግዚአብሔርን ማመስገን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?



(ለደቀመዝሙር አድራጊህ መልስ ስጥ)

1ኛተስ. 5:16-19 እና ኤፌ.5:18-20 ያለውን ክፍል አንብብ::

ከእግዚአብሔር ጋር ስለማናገረውም ነገርና ስለሌሎች ሰዎች በጸሎት መነጋገር ያስፈለገው ለምንድን ነው? (ለደቀመዝሙር አድራጊህ መልስ ስጥ) ፊልጵ.4:6-7 1ኛዮሐ.5:14-15

## ሕብረት

ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር እርስ በርስ እየተበረታታህና እየተጽናናህ ግንኙነት ማድረግ የምትችለው በሕብረት አማካኝነት ነው:: ዕብ.10:24-25 ያለውን ክፍል አንብብ::

ከሌሎች ጊዜያት ይልቅ ይህ ለአንተ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?(የሐዋ 2:37-47 ያለውን ክፍል በማንበብ ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩበት)

እግዚአብሔር አምላክ በማያቋርጥ ሁኔታ ክርስቲያናዊ ኅብረት እንፈልግ ዘንድ የሚጠብቅብን ለምንድን ነው?

(ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩበት)

የክርስቶስ አካል ከሁሉም አማኞች የተወጣጣ ነው (1 ቆሮ.12:14-27)::ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እውነት ለሚሰብክበት÷አማኞች ለሚበረታቱበትና ለአገልግሎት ለሚዘጋጁበት የአማኞች ቤተሰብ በሆነ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አስፈላጊነት ላይ ተኩረት ያደርጋል :: በዚህ የአማኞች ቤተሰብ ውስጥ እግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት የምናድገው :: እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኝበትና ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እርስ በርሳችን

ልንበረታታ የምንችልባቸው ጥቂት መንገዶች የሚከተሉት ናቸው:-

| | |
|---|---|
| • በወንድማማችነት ፍቅር እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ | ሮሜ.12:10 |
| • እርስ በርሳችሁ ለመከባበር ተሽቀዳደሙ | ሮሜ.12:10 |
| • እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ ተወካይ እንደመሆናችሁ መጠን የአንድነትን መንፈስ ይስጣችሁ | ሮሜ.15:5 |
| • ክርስቶስ እናንተን እንደተቀበላችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ | ሮሜ. 15:7 |
| • እርስ በርስ ተመካከሩ | ሮሜ. 15:14 |
| • ለክርስቶስ ክብር ብላችሁ ከእናንተ እያንዳንዱ ለሌላው ይታዘዝ | ኤፌ.5:21 |
| • አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል | ገላ. 5:13 |
| • እያንዳንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸክም | ገላ.6:2 |

ለሕብረት የግሪኩ ቃል «ኮይኒያ» በአማርኛ«ሽርክና ፣በጋራ መጠቀም የሚለውን ይተረጉምልናል:: እንደ ክርስቲያን በብዙ ዓይነት መንገዶች ሕይወታችንን ለሌሎች ማካፈልና ከሌሎችም መቀበል ይገባናል:: ያለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስቲያናዊ ሕብረት በእግዚአብሔር ላይ እናምፃለን፣ የመስጠትና የመቀባበልንም በረከት ዋጋ እናሳጣለን::

## መመስከር

ክርስቲያን ካልሆኑት ሰዎች ጋር ፍቅር እያሣየናቸውና ከክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነታችንና ሕብረታችን በቃል በማካፈል እየመሰከርንላቸው ልንግባባቸው እንችላለን::እንዲሁም ደግሞ ከእርሱ ጋር ዘላለማዊ ግንኙነት በክርስቶስ አማካኝነት መፍጠር እንደሚችሉ ልንመሰክርላቸው እንችላለን::

ሐዋ.18:4-12: 1ኛ ጴጥ.3:13-15÷18 ያለውን ክፍል አንብብ::

ለሌሎች ስለ ክርስቶስ ለመመስከር የሚያነሣሣህ ምንድን ነው? (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩበት)



በሕይወትህ ክርስቶስ ስላደረገው ነገር መናገር የምትፈልገው ለማነው? (የስማቸውን ዝርዝር ብትችል ለደቀመዝሙር አድራጊህ ተናገር::) ክርስቶስን ከጓደኞችህ ጋር በማስተዋወቅ ረገድ ልትረዳ ትፈልጋለህን? (ለደቀመዝሙር አድራጊህ ንገረው)

መጠቃለያ:-1ኛቆሮ. 3:6-7ን አንብብ::እግዚአብሔር የእድገትህ ምንጭ ነው:: መንፈሳዊ ብስለትን በግል ጥረት ልታመጣ (ልታሳድገው) አትችልም እግዚአብሔርን በምታመልክበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ፣መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ፣ጸልይ የክርስቶስን አዳኝነት ለሌሎች አካፍል:እንደዚሁም ከሌሎች አማኞች ጋር የሕብረት ጊዜ ውሰድ:: ይህ ጊዜ እግዚአብሔር በአንተ ሕይወት ፍሬንና ብስለትን እያስገኘ በሥራ ላይ ይሆናል::

3. <u>እንደ እግዚአብሔር ልጅ በምታድግበት ጊዜ ምን ይጠበቅብሃል?</u>

እግዚአብሔር በአንተ ሕይወት ውስጥ እንዲያፈራ የምትፈለገውን አንዳንድ ባሕርያትን በሚመለከት ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩበት::

ስለ መንፈሳዊ ብስለት ሥዕላዊ መግለጫዎች ሊሆኑ ስለሚችሉ ነገሮች አስብ:: (በ2ኛ ጴጥ. 1:5-9 ላይ አንብብና ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩበት)::

እንደዚህ ክፍል ሃሳብ ዋነኛው (ቀዳሚው) የመንፈሳዊ እድገት እንቅፋት ምንድን ነው? (ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ተወያዩበት)::

እንዴት ይቅር ለማለት እንዳለብን የሚያመለክቱትን በዝርዝር መመዝገብህን ቀጥል:: እነዚህ ሁሉ ደህንነትህን የይቅርታህን ምስክርነትና ሦስቱን ምሳሌያዊ ክቦች ለሌሎች በምስክርነት መልክ ለማካፈል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ::

- ለጎደኞችህ ምስክርነትህን ለማካፈል ትችል ዘንድ ምቹ ሁኔታዎችን ለማግኘት ደቀመዝሙር አድራጊህ እንዲፀልይልህ ጠይቀው::ለአንድ ሰው ከመመስከር በፊት ለፀሎት የጊዜ ዕቅድ አዘጋጅ ::ከደቀመዝሙር አድራጊህ ጋር ለምስክርነት መውጣት የሚሻል ከሆነ ከአንተ ጋር እንዲወጣ ጠይቀው::
- በትምህርት ሦስት ውስጥ ያለውን «በክርስቶስ ማዕ ከላዊነት የተመራ ሕይወት ሥዕላዊ መግለጫ» በመከለስ ለመሣልና ለሌላ ሰው ለማስረዳት ተዘጋጅ:: «በክርስቶስ ማዕከላዊነት የተመራ ሕይወት አመልካች ሥዕላዊ መግለጫን» ለብዙ ክርስቲያን ጎደኞችህ ስትገልጽ እንዲህ በል:: «ይህ ሥዕላዊ መግለጫ የክርስቲያን ደቀመዝሙርነትን ግብ ሕያው በሆነው በክርስቶስ የተነቃቃና የታደሰ ሕይወትን ይወክላል ትላለህ»:: ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ያስረከቡ ሰዎች ለቃሉ እና ለጸሎት ያለማቋረጥ ጊዜ ስለሚሰጡ የአብን ፈቃድ ለማወቅ እና ለማድረግ የተዘጋጁ ናቸው:: በክርስቶስ የሚመሩ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ያደርግ እንደነበር ሌሎች ክርስቲያኖችን ማየትና መቀባበል ሁል ጊዜ መልካሙን መመኘትና መዋደድ በደቀመዝሙርነትና በመልካም ሥራ ዎች ሕብረት አማካይነት መነቃቃት ያዘወትራሉ::



ሕብረታቸው እውነተኛ ሕብረት በመሆኑ ከምግብና ከጋራ ጊዜ ደስታ ያለፈነው:: አንዱ ለሌላው የሚለውን የመጽሐፍ ቃልን ለማሟላት እያንዳንዱ ለሌላው ተጠያቂ ይሆናል::

- በክርስቶስ ማዕከላዊነት ሕይወት የሚኖሩ ምዕመናን ያላመኑትን የሚያዩት ክርስቶስ እንደሚያያቸው ነው:: በመሆኑም ክርስቶስ ለኃጢአታቸው ይቅርታ በመስቀሉ ሞት ያደረገላቸውን መልካም የደህንነት ዜና ያበስሉላቸዋል:: ይህ ሕይወት እግዚአብሔር የሚከብርበትና የክርስቲያንን ሕይወትና ምስክርነቱን የሚያበረታታ ነው::
- ደቀመዝሙርህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ:- ይህ በክርስቶስ ማዕከላዊነት የተመራ ሕይወት የተሰኘው ስዕላዊ መግለጫ ሕይወትህን ይወክላል ወይ? ለጥያቄህ መልስ እንዲሰጥህ ለደቀመዝሙርህ ፍቀድለት:: ከዚያም በኋላ ይህ ሥዕላዊ መግለጫ ሕይወትህን የሚወክል እንዲሆን ትመኛለህ ወይ ብለህ ደቀመዝሙርህን ጠይቅ:: ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ሃይል የተሞላ ሕይወት የተሰኘውን በራሪ ጽሁፍ ግለጽለት:: ወይም የተሟላ ደቀመዝሙር የመሆንና የማድረግ እግዚአብሔርን በሕይወት የማወቅ ትምህርት በመከታተል የዚህ በረከት ተካፋይ እንዲሆን ጋብዘው::
- በጸሎት መንፈስ ሆናችሁ እግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ የተባለውን መሠረታዊ ደቀመዝሙርነት የምታስተምሯቸውን ሌሎችን ሰዎች ምረጡዋቸው:: በእናንተው አማካይነት ለራሳቸው ደቀመዝሙር ሆነው ሌሎችን ደቀመዝሙር ለማድረግ ብቁ እንዲሆኑ በየግላቸው ይዛችሁ

አስተምሩዋቸው:: ደቀመዝሙር በማድረግ ላይም እያላችሁ እያንዳንዳቸው ከራሳቸው ጋር 3 ሌሎች ሰዎች ደቀመዝሙር በማድረግ ሂደት መሰሎቻቸውን የሚያፈሩበትን ቀላል መንገድ አሳዩዋቸው::

- ደቀመዝሙር ተደራጊ አድራጊ በሚሆኑበት ወቅት ሁሉ እያንዳንዱን የተማሩትን ትምህርት ከመጀመሪያው ትምህርት ጀምሮ ለሌላው ደቀመዝሙር ተደራጊ አድራጊ የመሆን በረከትና ጥቅምን አስረዱዋቸው እንዲያደርጉም እርዱዋቸው::
- ደቀመዝሙርነት ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ባለማቋረጥ ዕድገት የተመሰረተ የሕይወት መመሪያ ትምህርትን መቀበልና ወዲያውኑ ለሌላው ሰው የማስተላለፍ ሂደት መሆኑን ለደቀመዝሙርህ አስረዳው::
- ደቀመዝሙርህ ሌላውን ደቀመዝሙር ማድረግ ወዲያውኑ ማካሄድ መተማመንን የተሰጠውን ታላቁን የወንጌል ተልዕ ኮን አደራ በሃላፊነት በመወጣት ደቀመዛሙርት አድርጓቸው:: የተባልንበትን ታላቁን ትዕዛዝ በመፈጸም መባ ረክን ያመስክታል::
- ደቀመዝሙርህ እንግዚአብሔርን በሕይወት ማወቅ የተሰኘ ውን ትምህርት 4ኛውንና የመጨረሻውን ሲደርስ ከመጀመሪ ያ ትምህርት ጀምሮ እስከ 4ኛው ድረስ እያንዳንዱን ትምህርት በትክክል መከታተሉንና በየትምህርቱ በሕይወት መተግበር የሚለውን ክፍል አጠናቅቆ ሌላውን ሰው ደቀመዝሙር በማድረግ ላይ ለመሆኑ እርግጠኛ ሁን::



- አስታውስ፡- በአራቱም ትምህርት አንተ የማታደርገውን ነገር ሌሎች እንዲያደርጉ ማስገደድ መንፈሳዊ ግብዝነት ነው:: ስለሆነም ከእግዚአብሔር ጋር ዕለታዊ አካሄድ የማድረግ የግል ጽሞና ጊዜን የክርስቶስ አዳኝነት መመስከርን የዳኑትንም ደቀመዝሙር ተደራጊ አድራጊዎች ማድረግህን ለራስህ ቀጥል::
- በአጠቃላይ አራተኛውን ትምህርት ከደቀመዝሙርህ ጋር በምትፈጽሙበት ቀን ሁሉ የሚከተሉትን ጉዳዮች አትዘንጋ:: እነርሱም፡- ደቀመዝሙር በመሆንና በማድረግ ወቅት የተገኘ ውን የሕይወትን ዘላቂ በረከት በማመስከት እግዚአብሔርን ማመስገን እንደ ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ጓደኛሞች በማናቸውም ጊዜና ምክንያት ባለማቋረጥ የጽሞና ጊዜ ለማካሄድ የክርስቶስን አዳኝነት ለመመስከርና ደቀመዝሙር በማፍራት ሂደት መስክ ላይ ለመገኘት የጋራ መንፈሳዊ ስምምነት ማድረግ ናቸው::

4. እንደ እግዚአብሔር ልጅ ማደግ

የክፍለ ጊዜው ትኩረት:-

ከክርስቶስ ጋር ባለህ ግንኙነት ማደግ በሦስት ዓይነት የግንኙነት መንገዶች መታዘዝን ያካትታል::

ዝግጅት:-

በትናንሽ ፊደል የተጻፉትን ጥቅሶች ከልስ

የግንኙነት መሠረት :-

እንደገና ግለሰቡ ፍላጎት አሳድረውብኛል ብሎ አስቀድሞ ስለጠቀሳቸው ነገሮች ጠይቅ::

ወደ ርዕሱ ሽግግር :-

የመንፈስ ሙላትን በሥራ ላይ ለማዋል ዕድል ነበረህ ወይ ? ብለህ ጠይቅ በመንፈስ ስለመሞላት አንዳች ጥያቄ ይኖረሃል ወይ?

የትምህርት ወረቀት መጠቀም:-

ይህ ክፍለ ጊዜ በጣም ወሳኝ ነው:: ምክንያቱም ደቀመዝሙር ለሆነው አዲስ ክርስቲያን በሦስት ቁልፍ አካባቢዎች ተሳታፊ ለመሆን በመንደርደሪያነት ያገለግላልና::

- ቀጣይነት ያለው እድገትና ከጌታ ጋር እርምጃ
- ሌሎችን ደቀመዝሙር ማድረግ
- በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስላለው ምስክርነት

1.------ ለነዚህ ጥያቄዎች ግለሰቡ የሚሰጠውን መልሶች የበለጠ የዕድገት እድሎችን ለመከታተል ስለተጠቃሽ የፍላጎት ደረጃ ምንጭ ይሰጠናል::



- ዮሐ. 17:3(እግዚአብሔርን ማወቅ )
- ማቴ.22:36-40 እግዚአብሔርን በእውነት የምንወድ ከሆነ ሌሎችን ትእዛዛት እናሟላለን::
- ዮሐ.14:21( የርሱን ትዕዛዝ መፈጸም )

2. ——— በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሥር ያሉትን ጥያቄዎች ከመጠየቅ በተጨማሪ በቃሉ ላይ ካለህ ልምድ ጥቅሙን ማካፈል ትችላለህ::

መጽሐፍ ቅዱስ :-

2ኛ ጢሞ. 3:16 -17

ማስተማር:- ስለእግዚአብሔር፣ ስለ ራሴና ስለሌሎች ማወቅ ያለብኝ

ተግሣጽ:- ከማመን ወይም ከማድረግ መቆጠብ ያለብኝ

እርማት:- በአሳቤ፣በዝንባሌዬና ወይም በምግባሬ መለወጥ ያለበኝ

ለጽድቅ ራስን ማስለመድ :- የእግዚአብሔርን ቃል ወይም የእርሱን ማነሳሳት በመታዘዝ ማድረግ ያለብኝ::

ጸሎት :-

እግዚአብሔርን ማመስገንና ማምለክ ያለብን ለምንድን ነው? (የኛ ጌታና እግዚአብሔር ምስጋናና ክብር እንዲሁም እክብሮትንና ኃይል ሊቀበል ይገባል:: የኛን አምልኮ አይፈልግም ነገር ግን አምላኪዎችን ይፈልጋል:: ማለትም ወደፊቱ በሚመጡበትና በሚያመልኩበት ጊዜ ሕይወታቸው ይለወጥ ዘንድ መንፈሳዊ እርምጃቸው ይጠነክር ዘንድ) እግዚአብሔርን የምናመስግነው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር እንድናመስግነው ይጠብቅብናል:: እግዚአብሔርን በማመስገን በእርሱ ላይ ያለንን መታመን እንገልጻለን :: (አለማመስገን የማያፈቅርን ልብ ይገልጻል::)

ለምን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና ስለ ሌሎች መጸለይ አስፈለገ? (እግዚአብሔር ስለእያንዳንዱ የሕይወታችን ዝርዝር ነገር ፍላጎት አለው ። አንዳችን ሌላውን እንድንወድና እንድንጠነቀቅለትም ይጠብቅብናል ። እርሱ ኃይል የሚለቀቅልን እንደፈቃዱ የጸለይን እንደሆነ ነው ።

ሕብረት:-

ዕብ.10:24-25 (ለፍቅርና ለመልካም ሥራ በጋራ የማበረታታት ሁኔታ ውስጥ መሆን)

ግለሰቡ ክረስቲያንን ሕብረት ከየት ማግኘት ይችላል ለሚለው ጥያቄ መልስ ከሰጠ በኃላ በአጥቢያ ቤተክርስትያን ውስጥ አይነት ያለው ህብረት በመፈለግ ረገድ የራስህን ልምድ ጥቀስ።

መመስከር:-

በምስክረነት ክፍል ስር ግለሰቡ እምነቱን ለማካፈል እንዲጀምር ተጽዕኖ ልናሳድርበት እንፈልጋለን ። ደቀመዝሙርህ የወንጌል ትራክት የማካፈሉን ሥራ ከአንተ ጋር እንዲለማመድ አድርግ።ስለክርስቶስ ከአንድ ሰው ጋር ለመነጋገር ካንተ ጋር እንደሄድ ጋብዘው።

እግዚአብሔር የእድገታችን ምንጭ በሚናገረው የማጠቃለያ ዐ ረፍተ ነገር ላይ ትኩረት አድርግ።

3.——እግዚአብሔር በግለሰቡ ሕይወት ውስጥ ስለሚያደርገው ነገር የመጠባበቅን ባሕርይ አንጸባርቅ ። እድገት የቀስ በቀስ ሂደት እንደሆነ በማስረገጥ አስረዳ ።

2ኛ ጴጥ.1:5-9 (የኃጢአታችንን ይቅር መባል መርሳት ወይም ዝቅ አድርጎ ማየት የእግዚአብሔር አስደናቂ ፀጋ በኛ ላይ)



4.—— የግለሰቡን ምላሽ በመመልከት ለእድገት ሦስት እድሎች ሂድባቸው።

የግለሰቡ የመስጠት ደረጃ ምንም ዐይነት ይሁን በማህበራዊ ኑሮ ሕይወት እንደገና መቼ መገናኘት እንደሚቻል ግልጽ መታመን ባለው ሁኔታ ፈጽም። ለጽሞና ክፍለ ጊዜ፣ለሌሎች ለመመስከሩ ሥራና ሌሎችን ደቀመዝሙር ለማድረጉ ሥራ ቀጣይነት ማበረታቻ ለመሥጠት ይህ ወቅቱ ሊሆን ይችላል።

አብሮ በመማሩ ክፍለ ጊዜ ስለ ተገኙት የተወሰኑት ጥቅሞች እና የሕይወት ለውጦች እንደዚሁም ከእነዚህ ትምህርቶች በመነሳት በሕይወትህ ማዛመድ ስለተቻለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እግዚአብሔርን በማመስገን ጊዜ ውን በጸሎት ደምድም።

## አንድ ለአንድ ደቀመዝሙር አድራጊዎችን የማፍራት ሳምንታዊ መርሐግብር

1ኛ ሳምንት: ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን ራዕይ ገጽ 1-19

2ኛ. ሳምንት ደቀመዝሙር አድራጊነትን መመሪያ አጠቃቀምና የጽሞና ጊዜ ገጽ 20-27

3ኛ. ሳምንት: ትምህርት 1- ከእግዚአብሔር ጋር መጀመር ከገጽ 28-43

4ኛ. ሳምንት: ትምህርት 2- ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ስለማድረግ ከገጽ 44-59

5ኛ ሳምንት: ትምህርት 3- ለእግዚአብሔር የመኖር ኃይል ከገጽ 60-76

6ኛ ሳምንት: ትምህርት 4- እንደ እግዚአብሔር ልጅ ማደግ ገጽ 77-94

ማሳሰቢያ: ለደቀመዝሙር ተደራጊ አዲስ አማኝ እያንዳንዱን ትምህርት ለ4 ሳምንታት መጠቀም ይቻላል::



## አንድ ለአንድ የወንጌል ምስክርነትና ደቀመዛሙርትን የማፍራት ሂደት በ12 ወራት ታማኝነት

| | ትምህርት | ትምህርት | ትምህርት | ትምህርት | ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ ወር | ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ታማኝ | ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ታማኝ | ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ታማኝ | ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ታማኝ | 3 |
| 2ወር | » | » | » | » | 9 |
| 3ወር | » | » | » | » | 27 |
| 4ወር | » | » | » | » | 81 |
| 5ወር | » | » | » | » | 243 |
| 6ወር | » | » | » | » | 629 |
| 7ወር | » | » | » | » | 2,187 |
| 8ወር | » | » | » | » | 6,561 |
| 9ወር | » | » | » | » | 19,683 |
| 10ወር | » | » | » | » | 59,049 |
| 11ወር | » | » | » | 177,147 | » |
| 12ወር | » | » | » | 531,441 | » |

ማሳሰቢያ:- ታማኝ ደቀመዝሙር አድራጊ ብንሆን በየወሩ 3 ደቀመዝሙር አድራጊዎችን ልናፈራ እንችላለን:: በ12 ወር ግን 531,441 ደቀመዛሙርትን ማፍራት እንችላለን::

## አሸናፊውን የክርስትና ሕይወትን ለመኖር በክርስቶስ ያለህን ማንነት መረዳት ወሳኝ ነው።

<u>እኔ ማን ነኝ</u>? ተቀባይነት ያገኘሁ ነኝ:-

1. ዮሐ. 1:12 የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ።
2. ዮሐ. 15:15 የክርስቶስ ወገን ነኝ።
3. <u>ሮሜ.5:1</u> ጽድቅናን አግኝቼአለሁ።
4. 1ኛ ቆሮ.6:17 ከጌታ ጋር በአንድ መንፈስ ተባብረያለሁ።
5. 1ኛ ቆሮ. 6:19-20 በዋጋ ተገዝቼአለሁና የእግዚአብሔር የግሉ ነኝ።
6. 1ኛ ቆሮ.12:27 የክርስቶስ የአካሉ ክፍል አባል ነኝ።
7. ኤፌ.1:2 ተቀድሺያለሁ።
8. ኤፌ. 2:18 በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የመቅተብ ዕድል አግኝቻለሁ።
9. ቆላሳይስ.1:14 ተዋጅቻለሁ ለኃጢአቴም ሁሉ ይቅርታ ተደርጎልኛል።
10. 10. ቆላሳይስ. 2:10 ከክርስቶስ የተነሳ ፍጹም ሆኜአለሁ። ድኛለሁ።

1. <u>ሮሜ.8:1-2</u> ከዘለዓለም ኩነኔ ነፃ ወጥቻለሁ
2. <u>ሮሜ.8:28</u> ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እረጋግጫለሁ።
3. <u>ሮሜ.8:31 </u>ከሚኮንነኝና ከሚቃወመኝ ሁሉ ነፃ ወጥቻለሁ።
4. 2ኛ ቆሮ.1:21-22 ከእግዚአብሔር መጽናትን፣መቀባትንና መታተምንም አግኝቻለሁ።
5. ቆላሳይስ.3:3 ከክርስቶስ ጋር በመሆን በእግዚአብሔር ውስጥ ተሰወርሁ።
6. ፊልጵስዮስ.1:6 እግዚአብሔር በኔ የጀመረውን መልንሙን ሥራ እንደሚፈጽመው ተረድቻለሁ።
7. ፊልጵስስ. 3:20 የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ ነኝ።
8. 2ኛ ጢሞቲዎስ.1:7 እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠኝም።
9. ዕብ. 4:16 በሚያስፈልገኝ ጊዜ ሁሉ ፀጋና ምህረት አግኛለሁ።
10. 1ኛ ዮሐ. 5:18 ከእግዚአብሔር የተወለድሁ ነኝና ክፉው በኔ ላይ ሥልጣን የለውም።
11. ኤፌ. 1:5 የእግዚአብሔር ልጅ ሆኛለሁ

<u>በመለያዬ የምታወቅ ነኝ።</u>

1. ማቴ.5:13- 14 እኔ የዓለም ጨውና ብርሃን ነኝ።
2. ዮሐ. 15:1-5 እኔ የእውነተኛው የወይን ግንድ ቅርንጫፍና በእር ለሚገኝ ሕይወት መጠቀሚያ ነኝ።
3. ዮሐ.15:16 እኔ የተመረጥሁና ፍሬ እዳፈራ የተላክሁ ነኝ።
4. የሐዋሥራ 1:8 የክርስቶስን አዳኝነት በግል መመስከር የሚገባኝ ነኝ።
5. 1ኛቆሮ.3:16 የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነኝ።
6. 2ኛ ቆሮ.5:17 እኔ የእግዚአብሔር የማስታረቅ አገልጋይ ነኝ።
7. 2ኛቆሮ.6:1 እኔ ከእግዚአብሔር ጋር የሥራው ተካፋይ ሠራተኛ ተደርጊያለሁ። (1ቆሮ.3:9)
8. ኤፌ 2:6 በሰማያዊ ሥፍራ ከክርስቶስ ጋር ተቀምጬአለሁ።
9. ኤፌ.2:10 የእግዚአብሔር መልካሙን ሥራ ለመሥራት የተፈጠርሁ ነኝ።
10. ኤፌ 3:12 ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው በነፃነትና በእምነት ነው።



## <u>ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መኖር</u>




| | |
|---|---|
| የክርስቶስ ማዕከላዊነት | ገላ 2:20 ዮሐ 15:5 ቆላ 1:27 |
| የእግዚአብሐር ማንነት (ባህርይ) | 1ኛ ዜና 29:10-13 ራዕ 4:11 ራዕ 15:3-4 |
| ከእግዚአብሔ ጋር ግንኙነት | 1ኛ ጴጥ 2:2 ኢያሱ 1:8 ፊል 4:6,7 |
| በመንፈስ የተሞላ ህይወት | 1ኛ ቆሮ 2:15-16 ኤፌ 5:18 ገላ 5:16-18 |
| ህብረት | ማቴ 18:20 ዕብ 0:24,25 1ዮሐ 1:3 |
| ፈተና | ሮሜ 6:13,14፣ ዕብ 2:18 ያዕ 1:13,14 |
| መታዘዝ | ዮሐ 14:21 ሮሜ 12:1,2፣ ሉቃ 6:46 |

# ደቀመዝሙር አድራጊ የወንጌል ማኅበርተኛነትን
# የማሰልጠን ስርዓተ ትምህርት

## ክፍል አንድ: ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን

1. ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን ራዕይ
2. አንድ ለአንድ ደቀመዝሙርነት
3. ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን አመራር
4. ደቀመዝሙር አድራጊ የቤተሰብ ሕብረት
5. ደቀመዝሙር አድራጊ ቤተክርስቲያን የጋራ አምልኮ

## ክፍል ሁለት: የወንጌል መልዕክተኛ ቤተክርስቲያን

1. የወንጌል ተልዕኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ራዕይ
2. ለወንጌል ምስክርነት የኢቫንጅ ኪዩብ አጠቃቀም
3. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተክርስቲያን ተከላ ስልት
4. ቤተክርስቲያንን ለወንጌል ተልዕኮ ማኅበርተኛነት ማንቀሳቀስ
5. በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሚሽንስ ዲፓርትመንት ማቋቋም

## ክፍል ሦስት: የማኅበረ ምዕመናን አመራር

1. ደቀመዝሙር አድራጊ መሪ መንጋውን ያውቃል
2. የቤተክርስቲያን መጋቢነት እና የማስተዳደር አገልግሎት
3. የቤተክርስቲያን አገልግሎቶችን ራስን ማስቻል
4. የቤተክርስቲያን አገልግሎቶችን በመስጠት ማገልገል
5. ለህብረተሰብ ፍላጎቶች የቤተክርስቲያን ድርሻ